
* የቦረዳው ድንቅ ዋሻ
* እንድድደስ ትባችሁ
* የሮማው መቶ አለቃና ቤተሰቦቹ
* እናስተዋውቃችሁ




* የሸቶው ብልቃጥ
* እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ
* ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት
* ታቦት

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org





© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

## ሐመር

መጀመሪያ ዓመት ቁጥር 1

ጥር 1985 ዓ.ም.

## ይዘት

1. ከአዘጋጁ ............................ 1

2. የማኅበሩ መልእክት ..................... 2

3. ደብዳቤዎቻችሁ ........................ 3

4. ትምህርተ ሃይማኖት

❖ ሦስትነት በአንድነት ............ 3

❖ ታቦት .......................... 6

5. ኪነጥበብ

❖ የበረዷው ድንቅ ዋሻ ........... 10

❖ ወላዲተ አምላክ (ግጥም). ...... 16

❖ እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ...18

❖ የሸተው ብልታጥ ................ 19

6. እናስተዋውቃችሁ ....................22

7. ክርስቲያናዊ ሕይወት

❖ ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ .......24

❖ በረከተ ወንጌል ....................26

❖ እንድደሰትባችሁ ..................29

❖ ማነው እውነተኛ ..................32

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ–ቅዱሳን በሥነ-ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ትምህርተ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# ከአዘጋጁ

አንድ ፈላስፋ እስኪ የምትፈቅደውን ተመኝ ቢሉት፥ «ለሕይወቴ የሚያስፈልጉኝን ማግኘት እመኛለሁ እነርሱም ያመት ልብስ፥ የዕለት ጉርስ፥ ከወንድሞች ጋር መወያየትና መዝናናት፥ የሥጋ ጤንነት፥ ክፉ ክፉውን ነገር አለማስታወስ ናቸው» አለ። በእርግጥም የፈላስፋው ምኞት ማለፊያና አሌ የማይባል ነው። ይህንን መጠይቅ ለወደፊት ደንበኞቻችን (ለሕዝበ ክርስቲያኑ) ሐመር ብታቀርብ እርግጠኞች ነን ሁሉም እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፥ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆነው፥ ከቃለ እግዚአብሔር እጦት የተነሳ የደረቀ ጉሮሮአችንን የሚያርስ፥ የተጠማች ነፍሳችንን የሚያረካ ከጥሩ ምንጭ የተቀዳ ማየ ሕይወት እንሻለን እንደሚሆን መልሱ።

ሐመርም ይህንን አስቀድማ ከእግዚአብሔር በተሰጣት ሀብተ ትንቢት አዕማደ ምድር ከተባሉ ከሐዋርያት ርቱዕ ሃይማኖት ከተባሉ ከሠለስቱ ምዕት እንዲሁም የእነርሱን አሠር (ፈለግ) ተከትለው ቤተክርስቲያንን ካገለገሉ ከሚያገለግሉ ቅዱሳን አበው ያገኘችውን ዕድፍ ጉድፍ የሌለበትን ንጹሕ ማየ ተዋሕዶ በወርቅ ዋንጫ ልታጠጣችሁ ወገብዋን ጠበቅ አድርጋ አሥራ ተንስታለች።

ተስፋ መስጠት ሰውን የሚያጠምዱበት የሰጪዎች መረባቸው ነው። ለጌቶችም መመስገኛቸው ናት። እንዲሁም ተስፋ በደመና መስጠት በዝናም ይመስላል ይባላል። ምክንያቱም ደመና ከዞረ በኋላ ሳይዘንም የሚበተን አለ። የሚያዘንምም አለ። እንደዚሁም ሁሉ የሚፈጸም ተስፋ አለ። የማይፈጸም ተስፋ አለና። ሐመር ግን አሳይታ የምትነሳ ደመና አይደለችም። ሁል ጊዜ ጊዜዋን ጠብቃ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መድኃኒተ ነፍስ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር የምታዘንም ደመና ነች እንጂ ለዚሁም የእናንተ የምእመናን ያላሰለሰ ተሳትፎ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ነው።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም የተባ ብዕራችሁን የሰላ አንደበታችሁን በሐመር ላይ እንድታሳዩ ከወዲሁ ስመ አምላክን ጠርተን አደራ እንላለን።

ለሁሉም ነገር የተለየ የየራሱ ሥራ አለው። ነገር ግን የልብ ሥራው የተወደደና የተመረጠ መሆን ነው እንዳለ መፍቀሬ ጥበብ አርስጣጣሊስ። የሐመር ልዩ ጥረቷም በምእመናን ዘንድ የተወደደችና የተመረጠች በጉጉት የምትጠበቅ ሆና መገኘት ነው።

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን።

ዋና አዘጋጅ ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ ዲያቆን እሸቱ ታደሰ ወ/አገኘሁ

✉ 80078/1283

☎ 12–34–25

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ
የማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት
MAHIBEKE KIDUSAN LIBRARY

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

«ሐመር» የተሰኘችውን ኦርቶዶክሳዊት መጽሔት የሚያነብ ሁሉ ማንነቷንና ምንጯን መጠየቁ የማይቀር ነው። ከዚያም አልፎ ማኅበሩስ ማነው? የሚለውን ጥያቄ በአእምሮው እንደሚያብሰለስል ግልፅ ነው።

ሐመር በማኅበረ ቅዱሳን የሥነ–ጽሑፍና መዝሙር ክፍል እየተዘጋጀች የምትወጣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መንፈሳዊ መጽሔት ናት። ማኅበረ ቅዱሳንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር መንፈሳዊ አገልግሎት የሚፈጸም ማኅበር ነው። ይህም ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀጥተኛ እምነት (ዶግማ)፥ ሥርዓት (ቀኖና) እና መንፈሳዊ ውርስ (ትውፊት) የያዙና ለተተኪው ትውልድ የሚደርስበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ በትምህርተ ወንጌል አገልግሎት ላይ የተሰማሩትን አባቶችና ወንድሞች ደቀመዛሙርትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችና ተመርቀው በሥራ ላይ ያሉትን የተዋሕዶ ልጆች ያሰባሰበ ማኅበር ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ ቅዱሳንን ያፈራች፥ በችግር፥ በመከራና በስደት ወቅት ለብዙ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳንና የመሳሰሉት) መጠጊያ የሆነች በተለይ ደግሞ የቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ልዩ ሀገር በመሆኗ፥ የእውነተኛውና የጥንታዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆችም መላእክት ለአፍታ እንኳን ሳያቋርጡ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ብለው የሚያመሰግኑትን፥ ቅዱሳን ነቢያት የተነበዩለትን፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማሩትን፥ ቅዱሳን ሰማዕታት የተጋደሉለትን፥ ቅዱሳን ጻድቃን ይህን ሥጋዊ ዓለም ያሸነፉበትን ሃይማኖት የሚያውቁበትና የቅዱሳንን አማላጅነትና ክብር የሚገነዘቡበት መድረክ በመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን ተብሏል።

ማንኛውም ሰው የራሱ እምነት ሊኖረው ይችላል። እውነተኛ ሃይማኖት ግን ከእግዚአብሔር በፀጋ ለሰው ልጅ የተገለጠች አንዲት ናት፤ እንጂ የሰው ልጅ በፈለገው ጊዜ እንደተመቸው የሚያመርተው ሸቀጥ አይደለም፤ የሚታደስ አሮጌ ዕቃም አይደለም። ለሥጋዊ ፈቃዱ እንዲያመቸው አድርጎ የሚቀርፀው መተዳደሪያ ደንብም አይደለም።

ስለዚህ የእውነተኛና የቀጥተኛ ሃይማኖት ተከታይ (ክርስቲያን) ነኝ የሚል ሁሉ እውነትን ከሐሰት፥ ብርሃንን ከጨለማ፥ ደግን ከክፉ፥ መልካም ሥነ ምግባርን ከመጥፎ፥ ቅድስናን ከርኩሰት፥ ጽድቅን ከኃጢአት፥ ክርስቶስን ከዲያብሎስ ለይቶ ማወቅና በሚታይ በሕይወት መግለጥ ወይም ማሳየት ያስፈልጋል።

ከዚሁ አንጻር ማኅበረ ቅዱሳን በሐመር አማካይነት ይህ ትውልድ የራሱን ሃይማኖትና ማንነት (Identity) አውቆ ከኃጢአት ተጠብቆ ቤተክርስቲያኑን ያገለግል ዘንድ እንዲነሳ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ጥንታዊቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚነሱ ነፍሳትና የሚናወጡ ማዕበላት የማይበግራት ሐመር (መርከብ) ናት። ይህም ነፋሳት የሚገስፅ፥ ማዕበላትን ፀጥ የሚያደርግ መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ በውስጧ መኖሩን ያረጋገጠባትና የሕያው ቃሉ መዝገብ በመሆንዋ ይታወቃል። ዛሬ ማኅበረ ቅዱሳንም ይህ ትውልድ በዚህች ሐመር ውስጥ እንዲገባና ራሱን በንጽሕና ቀድሶ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖር አጥብቆ ያሳስባል። በሐመሯ ውስጥ ከገባ በኋላ ማንንቱን ዘንግቶ ወጥቶ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚነፍሰው ነፋስና በሚነሳው ማዕበል ተነጥቆ በጥልቅ ባሕር ውስጥ እንዳይሰጥም ያስገነዝባል።

በአጠቃላይ ማኅበሩ ይህ ትውልድ ኃጢአቱን ሁሉ በንስሐ ታጥቦ በንጽሕናና በቅድስና በዚህች ሐመር (ቅድስት ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ እየኖረ ዘለዓለማዊ የሕይወት ምግብን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀብሎ የማያልፈውን አምላካዊ መንግሥት እንዲወርስ ይጋብዛል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

MAHIBERE KIDUSAN LIBRARY

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

## ድቡዳቤዎቻችሁ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የማኅበረ ቅዱሳን ሥነ ጽሑፍና መዝሙር ዝግጅት ክፍል ይህችን የመጀመሪያው የሆነችውን አነስተኛ ኦርቶዶክሳዊ መጽሔት ሲያዘጋጅ ታላቅ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማዋል። ለዚህ ያበቃው እግዚአብሔርንም ያመሰግናል። ለወደፊቱ በአምላክ ቸርነት በዚሁ እንደሚቀጥል ሙሉ ተስፋ አለው።

ሆኖም ከአንባብያን ገንቢ አስተያየቶችን፥ መንፈሳዊ ሥነ–ጽሑፎችና ከሃይማኖት (ከእምነት) ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመላክ እንዲተባበሩ ብዙ ይጠበቃል።

ስለዚህ መጽሔቷ የጋራችን ስለሆነች እርስዎም ለዚህ ጥሪ አስተዋፅኦ ማድረግዎን አይዘንጉ። መልእክትዎን ለማስተናገድ ዝግጁዎች ነን።

### አድራሻችን


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የማኅበረ ቅዱሳን መጽሔት ዝግጅት ክፍል

✉ 80078 (1283)

☎ 12–34–25

አዲስ አበባ


ለዛሬ ግን እኛ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንጠይቃችሁ።

ሀ. የዛሬ ሳምንት ዓርብ ቀን፥
ትልቅ ነጭ በግ አረደን፥
የታመሙ ሁሉ መላው ዳኑ፥
በሥጋውና በደሙ።

ለ. የእኔ ቤት እዚህ ሳለልሽ፥
ለምን ምድረ ግብፅ ወረድሽ፥
ማልደሽ ይዘሽ ነይ ልጅሽን፥
ሰምት አደራሽን።

ሐ. ከእናቱ በፊት የተወለደ፥
ከእናቱ በፊት ጡት የጠባ ማነው?

# ትምህርተ ሃይማኖት


በብርሃኑ ጐበና


ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) የምንማርበት ይሆናል። ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) ስንል ስለ እግዚአብሔር ህልውና፥ ስለማይመረመር ባሕርዩ፥ ስለ ልዩ ሦስትነቱ፥ ስለ መለኮታዊ አንድነቱ፥ ሰው ስለሆነበት እፁብ ድንቅ ምሥጢሩ ከእዚህ ሕያው አምላክ በጥምቀት የመወለዳችን ምሥጢር የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው።

እግዚአብሔር ምሉዕ ስፉህ የሆነ በዘመኑ ሸረት በመንግሥቱ ሕልፈት የሌለበት ገናና አምላክ ነው። ክርስቲያኖች ይህን ታላቅ አምላክ የምናመልክ ለእርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም የምንገዛለት ነው። የምናመልከው እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ባሕርዩ እንዴት ነው? እንዴትስ እናመልከዋለን? የሚሉትን ጥያቄዎች የምንመልሰው ትምህርተ ሃይማኖትን ጠንቅቀን ያወቅን እንደሆን ነው።

እግዚአብሔርን አወቅነው፤ አመለክነው የምንለው ስለ እርሱ ማንነት በንጹህ ልባችን ስናውቅና ስንረዳ ነው። የእግዚአብሔርን መኖር የሚያስረዱን ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓትና አሠራሩ፥ የኅሊና ምስክርነት፥ የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ፥ የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት ናቸው።

የእግዚአብሔር ባሕርይ ደግሞ፥ መንፈስነት፥ ዘላለማዊነት፥ ሁሉን ቻይነት፥ አለመለዋወጥ፥ ምሉዕነት፥ መለኮታዊ ጥበቃው፥ አዋቂነቱና ጥበቡ፥ ቅዱስነቱ፥ ደግነቱና የማንንም ዕርዳታ አለመፈለጉ የመሳሰለው ሁሉ ነው።

ለዛሬው የዚህን ታላቅ አምላክ አንድነትና ሦስትነት መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገን እንማራለን። ለሐዋርያት ምሥጢሩን የገለፀ አምላክ ለእኛም ይግለጽልን። አሜን

## ሦስትነት በአንድነት

ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት ነው። (በግዕዝ) ምሥጢረ ሥላሴ (የሦስትነት ምሥጢር) ማለት ደግሞ ሦስት ከዊን (ሁኔታ) ያለው መለኮት ቅድመ ዓለም በነበሩ ዛሬም ባሉ ዓለምን አሳልፈው በሚኖሩ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በተባሉ በሦስት አካላት እንዳለ መርምሮ አውቆ እግዚአብሔር በስም፥ በገጽ፥ በአካል ሦስት፤ በባሕርይ፥ በሕልውና፥ በመለኮት አንድ ብሎ ማመን ነው[1]።

ይህን እምነት (ዶግማ) የማይቀበሉና እግዚአብሔርን አንድ ገጽ አንድ አካል ብለው የሚያምኑ አሉ። ለምሳሌ ሳበልዮሳውያን፤ ሳበልዮስ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የሊቢያ ሰው ነው። በትምህርት ምክንያት ወደ ሮም ሄዶ በዚያም እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ ገጽ ነው የሚለውን ትምህርት ተማረ።




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ይህን የተማረው «አብ መከራ ተቀበለ» ከሚሉ መናፍቃን ነው። እነዚህ መናፍቃን በሮም ያስተምሩት የነበረው «ሞደሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም (Modalistic Monarchianism)» ይባላል። አንዱ ገጽ በተለያዩ ዘመናት ቅርጹን ለዋውጦ ታየ ማለት ነው። ሰባልዮስ ይህን ሁሉ አግበስብሶ ወደአገሩ ተመለሰ፥ ይህንኑም ማስተማር ጀመረ። ሰባልዮስ እንደሚለው አንዱ አካል እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን ስለሠራ አብ ተባለ፥ በዘመነ ሥጋዌ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ስለታየና ሐዲስ ኪዳንንም ስለሰጠን ወልድ ተባለ። ኋላም በበዓለ ጰንጠቆስጤ በአምሳል እሳት ወርዶ ለሐዋርያት ምሥጢር በመግለጡ ቋንቋ በማናገሩ መንፈስ ቅዱስ ተባለ እንጂ አምላክ አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ይል ነበር[2]።

በአሁኑ ጊዜ የሥላሴን ትምህርት የሚቃወሙ አንዳንድ ክፍሎች አሉ። እነዚህ ክፍሎች አምላክ ሥላሴ እንዳልሆነ በድፍረት ይናገራሉ። እንዲያውም የሥላሴ ትምህርት ጥንተ መሠረቱ ከጥንት ባቢሎናዊያን፥ ከለዳውያን አምልኮት የተኮረጀ አድርገው ያስተምራሉ። ጥንት ባቢሎናዊያን የዛሬ 2200 ዓ.ዓ. ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስት አማልክት ያመልኩ ነበር። ኩሽ (Cush) አባት፥ ሴምራሚስ (Semiramis) እናት የኩሽ ሚስት መሆንዋ ነው እና ናምሩድ (Nimrod) የመጀመሪያው የባቢሎን ገዥ የሴምራሚስ ልጅ በኋላ ግን ባልዋ የሆነ። እነዚህ ሦስቱ በባቢሎናዊያን ዘንድ እንደ ፈጣሪ ይታዩ ነበር። ስለዚህም የክርስትናውም ዓለም የሥላሴን ትምህርት ከጥንት ባቢሎና ዊያን የኮረጀው እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ ትምህርት አይደለም ይላሉ። ሌላም ማስመሰያ ያቀርባሉ፥ በሂንዱ እምነት የሥላሴ እምነት አለ ይሉና ይህን ይጠቅሳሉ፥ ብርሐማ (Brahma) ፈጣሪ፥ ቪሽኑ (Vishnu) ጠባቂ እና ሲቫ (Siva) አጥፊ። እነዚህ ሦስቱ በአንድነት አንድ አምላክ ብርሐም (Brahm) ይባላሉ። ይህን ጠቅሰው የሥላሴ ትምህርት ከዚህ የተቀዳ ከንቱ ባዕድ አምልኮ ነው ይላሉ[3]።

አፅራረ ሥላሴ ከላይ በገለጽነው መሠረት የሥላሴ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልሰፈረ እንዲያውም ከአሕዛብ ባዕድ አምልኮ ጋር የተሳሰረ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል። በእርግጥ የሥላሴ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈ ሆኖ ነው? ወይስ ለክህደታቸው ማስተባበያ ሲሉ ያቀረቡት ነው? ለማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ ይመስክር።

ኦሪት ዘፍጥረት 1፥26 «እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ከዚህ አባባል የምንረዳው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር አንድ ገጽ እንዳልሆነ ነው። እግዚአብሔርም አለ ብሎ አንድነቱን ሲገልጽ፥ «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ሲል ደግሞ ሦስትነትን ያመለክታል።

ተቃዋሚዎች እግዚአብሔር ራሱን በአክብሮት ለመጥራት ብሎ በነገሥታት ሥርዓትና ልምድ እራሱን አብዝቶ ተናገረ እንጂ ሦስት አካላት መሆኑን ሊገልጽ ፈልጎ አይደለም ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ንጋትና እውነት እያደር ይጠራል እንደሚባለው ሁሉ እነርሱም ለጊዜው እውነትን ትቢያ ያለበሱ መስሎአቸው ይህን የሐሰት ምክንያት ቢያቀርቡም የትም አያመልጡም። እነርሱ እንደሚሉት በጥንት ነገሥታት ዘንድ ይህ ዓይነት ዘይቤ አንዱ ንጉሥ ራሱን «እኛ» ብሎ መጥራት እንዳልነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው እውነታ ነው። ለዚህም እነዚህን ምሳሌዎች እንጥቀስ:-

ፈርኦን ዮሴፍን «በግብፅ ምድር ሾምኩህ» አለው እንጂ ሾምንህ አላለውም። ዘፍ.41፥41።

«እኔ ዳርዮስ ይህንን አዝዣለሁ» እንጂ አዘናል አላለም። መጽ.ዕዝ. 6፥12።

«ናቡ ከደነጾርም የሕልሙን ፍቺ እንዲያስታውቁኝ የባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ ይገቡ ዘንድ አዘዝሁ» አለ እንጂ አዘዝን አላለም።ትን.ዳን. 4፥6።

እንግዲህ ነገሥታቱ ከእግዚአብሔር ይህን አብነት ነስተው ራሳቸውን ለማክበር እኛ ማለት ከጀመሩ እነ ፈርኦን፥ ዳርዮስ፥ ናቡከደነጾርም ይህን ዘይቤ ሲጠቀሙበት በተገኙ ነበር።

ነገር ግን እግዚአብሔር የተናገረው ራሱን ለማክበር ብሎ ሳይሆን ሦስትነቱን ሊገልጽ ሽቶ ነው። ይህንም ከዚህ ቀጥለን የበለጠ ጉልህ አድርገን እናስረዳለን።

እዚህ ላይ ሦስት መሆናቸው እኮ አልተገለጸም ሁለትም ሊሆኑ ይችላሉ፥ እግዚአብሔርና ሚካኤል ሊሉም ይችላሉ። ተጠራጣሪዎች የሥላሴን ትምህርት ለመቃወም ብለው ሁለትነትን እንጂ ሦስትነትን አያመለክትም ካሉ በሌላ ጥቅስ ከሁለት በላይ መሆናቸውን እስክናረጋግጥላቸው ድረስ እግዚአብሔርና ሚካኤልን ሲጠቁም ነው የሚለው አባባላቸውን ግን የሐሰት ትምህርት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ያሻል።

ለመሆኑ እግዚአብሔርን በመልክ የሚመስለው፥ በባሕርይ የሚተካከለው ከመላእክት ወገን አለ? ከሌለ እንዴት ታዲያ (እግዚአብሔር) ራሱን ከሚካኤል ጋር ደምሮ አስተካክሎ በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር ሊል! ሚካኤልን (ፍጡሩን) አማካሪ፥ ረዳት አደረገ? የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል። «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? እውቀትን ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?...» (ኢሳ.40፥13) መልሱ ማንም ምንም የሚል እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። ብርሃነ ዓለም ጳውሎስም «የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና» (ሮሜ.11፥34–36) በማለት የተጠራጣሪዎቹን አባባል ያከሸፈዋል። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ያማከረው ፍጥረት የለምና እንፍጠር ያለው በአንድነት፥ በሦስትነት የሚሠለስ፥ የሚቀደስ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዘፍ.3፥22 «እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፥» ሁለት የሚለውን አመለካከት ይህ አባባል ሙሉ በሙሉ እንደሚያፈርሰው እናያለን። ከእኛ የሚለው ቃል ከአንድ በላይ መሆኑን ግልጽ ሲያደርግልን እንደ አንዱ የሚለው ደግሞ ከሁለት በላይ ሦስት መሆኑን ያረጋግጣል። ምክንያቱም ሁለት ብቻ ቢሆኑ ኖሮማ ተናጋሪው እንደ አንተ ወይም እንደ እኔ ማለት ነበረበት እንጂ እንደ አንዱ ብሎ ባልተናገረ ነበር።

ዘፍ.11፥6–7 በዚህ ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር «ኑ እንውረድ» ማለቱ ሦስትነትን ሲያመለክት ነው። አሁንም ሁለት ብቻ ቢሆኑ ኖሮ ና እንውረድ ማለት ነበረበት። መላእክቱን ነው ኑ እንውረድ ያለው የሚል ሰበብ የሚያቀርቡ ከሆነም እግዚአብሔር ንጉሠ ሰማይ ወምድር ነውና «ሂዱ ውረዱ» ብሎ ያዛቸው ነበር እንጂ ራሱን ከመላእክት ጋር ደምሮ ኑ እንውረድ ሊል አይችልም። ባሕርይው አይደለምና። ደግሞም ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ አማካሪና አጋዥ አይፈልግም። ጥቅመ ሰናአርን (የሰናዖርን ግንብ) ለማፍረስ የመላእክቱን እገዛ ሽቶ ኑ እንውረድ አለ ብሎ ማመን እግዚአብሔርን እንደመሳደብ ነው። ባሕርያዊ ኃይሉንም እንደ መካድ ነው።

ዘፍ. 18፥1–15 እግዚአብሔር ለአብርሃም በተገለጸለት ጊዜ በሦስት ሰዎች አምሳል ነበር ይህም ሦስትነቱን ሲያሳውቀው ነው። ሙሴ ለይቶ እግዚአብሔር ተገለጠለት ብሎ ተና ገረ እንጂ መላእክት ተገለጡለት አላለም። አብርሃምም በፊቱ ያሉት የሚያያቸው ሦስት ሆነው ሳለ «አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ» ማለቱ አንድነቱን ሲገልጽ ሲሆን «ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ» በማለቱ ደግሞ የአካላትን ሦስትነት ገለጸ።

ይህን ግልጽና የማያከራክር ማስረጃ እያዩ እንኳን ተጠራጣሪዎች አያምኑም። መቼም አባቶች እንደ ሚሉት «ከትምባሆ ልምላሜ ከመናፍቅ ትርጓሜ» አይጠፋምና እነርሱም ሌላ ምክንያት ይሰጣሉ። ለአብርሃም የተገለጡለት እኮ ሥላሴ ሳይሆኑ ሁለት መላእክትና እግዚአብሔር ናቸው ይላሉ። በመሠረቱ ሙሴ እነርሱ እንዳሉት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ከመላእክቱ ጋር ለአብርሃም ተገለጸለት ብሎ በጻፈ ነበር። ጻፉ ግን እርሱ እግዚአብሔር ተገለጠለት ብሎ እግዚአብሔር በሦስት ሰዎች አምሳል እንደተገለጸለት ጻፈ። ስለዚህ ክርስቲያኖች የተጻፈን እንጂ ያልተጻፈን ማንበብ ስላለመደብን ከልቡናቸው አንቅተው የሚናገሩትን ጆሮአችን አንጥሮ ይመልሰዋል እንጂ አይሰማውም።

ከምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ጋር ምዕራፍ አሥራ ስምንትን በማጣመር ከላይ የገለጹትን አባባላቸውን አማናዊ ለማስመሰል ይሞክራሉ። በምዕ 18፥22 «ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር» የሚለውን ጠቅሰው በማውጣት «ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ» ከሚለው ጋር አቆራኝተው ለአብርሃም ከታዩት ሦስት ሰዎች ሁለቱ መላእክት መሆናቸውን በከንቱ ለማሳመን ይጥራሉ።

በመሠረቱ ለአብርሃም የተገለጹለት ሥላሴ እንደመሆናቸው ሰዎቹ የሚለው ቃል ሥላሴን የሚጠቁም ነው። ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሄዱ ሲል ሥላሴን ማለቱ ነው። ፊታቸውን አቀኑ ሄዱ ማለቱ መሄድ መምጣት፥ መውጣት፥ መውረድ (እንደ ውሱን አካል) ኖሮባቸው አይደለም፥ ሃሳባቸውን (ንግግራቸውን) በሰዶም ላይ አደረጉ ማለት ነው። አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር ሲል ደግሞ ሥላሴ ሰዶም በእሳት መጥፋት እንዳለባት መወሰናቸውን ሲነግሩት አብርሃም ግን ስለ ሰዶም ሊያማልድ በባለሟልነት ተገኝቶ ነበር ማለት ነው። ሁለቱም መላእክት የሚለውም ከሦስቱ ሁለቱ ማለት ሳይሆን ታዋቂ የሆኑት መላእክት ሚካኤልና ገብርኤል ሰዶምና ገሞራን እንዲያጠፉ መታዘዛቸውን የሚያስረዳ ነው። (የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ይመልከቱ)።

አሪት ዘኁልቁ 6፥24–36 «እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፥ እግዚአብሔር የፊቱን ብርሃን ይግለጥልህ ይራራልህም፥ እግዚአብሔር በምህረት ዐይን ይመልከትህ ሰላሙንም ይስጥህ» ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ብሎ መጥራቱ ያለምክንያት አይደለም ወይም አላስፈላጊ ድግግሞሽ ለመፍጠር አይደለም። ባጭሩ እግዚአብሔር ብሎ ሌሎቹን ቃላት ብቻ መደርደር ሲችል ስመ እግዚአብሔርን ወስኖ ሦስት ጊዜ መጥራቱ ሦስትነትን ሲያመለክት ነው።

መዝሙር 117 (118)፥ 16 እና 17 «የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች»

አሁንም የእግዚአብሔር ቀኝ የሚ ለው ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅ ሷል። እንዲያውም ከመካከለኛው በስተቀር የመጀመሪያውና የመጨ ረሻው አንድ ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ናቸው። ልበ አምላክ ዳዊት ይኸን ሊል የቻለው ምክንያት ስላለው ነው። የአምላክን አንድነትና ሦስትነት ሊያስተምር ፈልጎ ነው። የአምላክን ሦስትነት ለመግለጽ ከታሰበ ታዲያ ሦስቱም አንድ ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ለምን አልሆኑም? የመካከለኛው ለምን ተለየ? የሚል ጥያቄ ካነሱም ያም ቢሆን ሆን ተብሎ የተነገረ ነው። ምክንያቱም ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ እንደሚ ወለድና በኃጢአት ተጐሳቁሎ ክብሩን ተገፎ በመንጸፈ ደይን ወድቆ የነበረ አዳምን ከወደቀበት አንሥቶ ወደ ቀደመ ክብሩ እንደሚመልሰው በመን ፈስ ቅዱስ ስለተገለጸለት «የእግዚአ ብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ» ብሎ ወልድን ጠራ። የላይኛውና የታችኛው አንድ ዓይነት ዓረፍተ ነገር መሆና ቸው፥ አብና መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካላቸው ሥጋን አለመዋሐዳቸውን ለማመልከት ነው። ✣

ይቀጥላል

---

ምንጭ

1. ኵኵሐ ሃይማኖት ገጽ 103
2. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 72
3. Jehovah's Witnesses p.45
4. መጽሐፍ ቅዱስ

# ታቦት

ከአባ ወ/ትንሣኤ አያልነህ

ታቦት ቃሉ የግእዝ ነው።

ታቦት – በኮፕት (በግብፅ) ቴቢ፥ በዕብራይስጥ ቴባ (ቴቡታ)

በዐረብኛ ታቡት ይባላል። በግእዙ ግን ታቦት ነው የሚባለው።

ታቦት – ማለት የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ የእግዚአብሔር የክ ብሩ ዙፋን ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ በታቦቱ ላይ ሆኖ ሙሴን እንደ ሚያነጋግረው ራሱ እግዚአብሔር ለሙሴ ስለነገረውና በታቦቱም ላይ ሆኖ ስላነጋገረው ነው። ዘጸ.25፥22 ዘኁ.7፥89። ታቦት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነው። ዘጸ. 25፥1–22። ታቦት ለመጀመ ሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሠራው ከግራር እንጨት ነው። «ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን፥ ይላልና፥ ዘጸ.25፥10 በውስጥና በውጭ በወርቅ እንዲለበጥ እግዚአብሔር አዟል።

ዘጸ.25፥11። ሙሴም እንደታ ዘዘ አድርጓል። ዘጸ.37፥1–3። ታቦቱንና በታቦቱ ዙሪያ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት እንዲሠራ የተፈቀደለ ትና የሠራ፥ እግዚአብሔር የመንፈስ ብልሃትን፥ ጥበብን ዕውቀትንና ማስተ ዋልን ሁሉ የሰጠው፥ እግዚአብሔር እራሱ የመረጠው ባስልኤል ነበር ዘጸ.31፥1-7።

በታቦቱ ውስጥ አሠርቱ ቃላት የተ ጻፉባቸው ሁለቱ ጽላቶች ነበሩ፥ ዘጸ.40፥20 ጽላት ማለት ቅዱስ ቃሉ የተጻፈበት ቅዱስ የድንጋይ ሰሌዳ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጽላቶች ሙሴ በሲና ተራራ 40 ቀንና 40 ሌሊት እህል ውኃ ሳይቀምስ ከጾመ በኋላ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበላቸው ናቸው። ዘጸ. 32፥ 15–21።

እስራኤል ሙሴ ከሲና ተራራ እስኪመለስ 40 ቀን መታገሥ አቅቷቸው አሮንን አስገድደው ጣዖት ሠርተው ሲሰግዱ አገኛቸው፥ በዚህ ጊዜ ሙሴ ለአምላኩ ቀናኢ ነውና ጣዖትን በማምለካቸው እጅግ ስለተ ናደደ አሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸውን ሁለት ጽላቶች ከተራራው በታች በም ድር ላይ ሠባበራቸው ዘጸ.32፥19። በዚህ ቸርና መሐሪ ምህረቱም ለዘለዓለም የሆነ አምላክ፥ ሙሴን ካጽናና ካረጋጋም በኋላ የሠበርካ ቸውን አስመስለህ አንተ ራስህ ሥራ እኔም እባርክልሃለሁ አለው። ሙሴ እንደታዘዘ አስመስሎ ሠራ፥ እግዚአ ብሔርም ባረከለት። ሙሴ ራሱ የሠራ ቸውን ሁለቱንም ጽላቶች፥ እንደታ ዘዘ በታቦቱ ውስጥ አስገባቸው። ዘጸ.34፥1–10። ዘጸ.40፥20።

ይህም ታቦት በሙሴ ድንኳን ውስጥ ተቀምጦ፥ እግዚአብሔር አም ላክ በዚያ ክብሩን እየገለጠ፥ እሥራኤልም በድንኳኑ ደጃፍ በታ ቦቱ ፊት ለፊት ለእግዚአብሔር ስም እየሰገዱ፥ እግዚአብሔርን እያመ ለኩ፥ ለስሙ እየዘመሩ የአምልኮ ሥርዓታቸውን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቀጥለው ሕይወታቸው በደስታና በሰ ላም ይኖር ነበር። ሙሴ ሞቶ ኢያሱ እሥራኤልን ለመምራት ተተካ። በምድረ በዳ እሥራኤልን እየመራ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ፥ ድንገት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶበት እሥራኤልን የሚያሻግርበት ድልድይ አጣ።

ኢያሱ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፥ እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፥ ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ይሂዱና የሞላውን ወንዝ ይርገጡት ወንዙም ከሁለት ይከፈላል፥ መሐሉም ይደርቃል፥ እሥራኤል በሰላም ይሻገራሉ፥ ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ ጨርሰው እስኪሻገሩ ድረስ ታቦቱን የተሸከሙ ካህናት ከወንዙ እንዳይወጡ። እነሱ የሚወጡት መጨረሻ ነው አለው። ኢያሱም እንደተባለው አደረገ። በታቦቱም አማካኝነት እግዚአብሔር አምላክ የሞላውን የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍሎ አሻገራቸው ታቦቱ የእግዚአብሔር ኃይል መግለጫ ነውና። መጽ.ኢ. 3፥1–እስከመጨረሻው።

ኢያሱ እሥራኤልን እየመራ ኢያሪኮ ደረሰ። ነገር ግን አሕዛብ የኢያሪኮን ዙሪያ ጽኑ በሆነ ግንብ አጥረው በሩን አንድ ብቻ አድርገው፥ በከባድ ኃይል በሩ እየተጠበቀ በውስጡ አሕዛብ ይኖሩ ስለነበርና፥ እሥራኤልም መግቢያ ስላጡ የእሥራኤል መሪ ኢያሱ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፥ እግዚአብሔርም ሰማውና እንደተለመደው ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው፥ ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በታቦቱ ፊት ለፊት እየነፉ 6 ቀን ይዙሩት በ7ኛውም ቀን ይፈርሳል አለው። እንደተባለው አደረገ፥ የኢያሪኮም ግንብ እንደ እንቧይ ካብ እንደ ክረምት ገደል ተናደ። ኢያሱ 6፥1–22 ኢያሱም ሰልፈኞቹን ይዞ ገባ፥ ጠላትን ሁሉ ጨረሰ፥ ርስትንም ለእሥራኤል አካፈለ ጋለሞታይቱ ረዓብም ከሞት የዳነች በዚህ ጊዜ ነበር። ዕብ.1፥31

እንግዲህ ይህ ታቦት የዮርዳኖስን ወንዝ ከፈለ፥ የኢያሪኮን ግንብ አፈረሰ፥ እግዚአብሔር የኃይሉ መግለጫ አደረገው ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ ክብሩንና ኃይሉን በታቦቱ ላይ እየገለጠ፥ እሥራኤልን እንደ ባልንጀራ እያነጋገረ እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር አብሮ ይኖር ነበር።

በዘመነ መሣፍንት ካህናቱም ሆኑ እሥራኤል እግዚአብሔርን በደሉ፥ በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን በጠላትነት ተነሥተው፥ ብዙ እሥራኤልን በሰይፍ ፈጁ ካህናቱንም ገደሉ። ታቦቱንም ማርከው ወሰዱ ወስደውም ከንቀታቸው የተነሣ አምላካችን ብለው ከሚጠሩት ዳጎን ከሚባል ጣዖታቸው ሥር አስቀመጡት።

ነገር ግን በታቦቱ ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል ስለነበረ የፍልስጥኤማውያን ጣዖት ዳጐንን አንኮታኩተው እጅ እግሩን ቆራረጠው። ይኸም በተደጋጋሚ ሦስት ጊዜ ሆነ። በተጨማሪም በታቦቱ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል በፍልስጥኤማውያን ላይ ተደራራቢ መቅሰፍትን ለቀቀባቸው። በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ሳይወዱ በግድ ታቦቱን ወደ አገሩ ወደ ኢየሩሳሌም መለሱ። 1ኛሳሙ.5፥1 ፍጻሜውና ምዕ.6።

ታቦቱ ወደ አገሩ ሲመለስ ዳዊትና ሕዝቡ ሁሉ በእልልታና በሆታ ተቀበሉት፥ በዚህ ጊዜ አንድ ዖዛ የተባለ እሥራኤላዊ ክህነት ሳይኖረውና ሳይፈቀድለት በድፍረት ታቦቱን በመንካቱ ወዲያውኑ ተቀሰፈ። 2ኛ.ሳሙ.6፥6–9። በዚህም በእግዚአብሔር ስም የተጠራውን እግዚአብሔር ያከበረውን ነገር ሁሉ እንጨት ነው፥ ድንጋይ ነው፥ ሥዕል ነው ብለን መናቅና ማቃለል እንደሌለብን እንረዳለን፥

ሕዝበ እሥራኤል ታቦቱን ለማክበር ሲሉ፥ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ሲሄዱ ሕዝቡ ከታቦቱ 2ሺህ ክንድ ያህል ይርቁ ነበር ኢያሱ.3፥4 ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ምዕመናን ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ ከታቦቱ ራቅ ይበሉ የሚባለው ከዚህ የተነሳ ነው።

ሰሎሞን ታላቁን ቤተ መቅደስ ሲሰራ ታቦቱን በታላቁ ቤተ መቅደስ ውስጥ በክብር አስቀምጦታል። 1ኛ ነገ. 8፥6 ከዚያም አገልግሎቱን ቀጥሏል። የዚህ ታቦት ክብር በሐዲስ ኪዳን በሰማይ ታይቷል። ራእ.11፥19።

በሐዲስ ኪዳን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን ባርኮ ቀድሶና አጽድቆ ሰጥቶናል። ማቴ. 21፥12–13 ማር. 11፥15–18። ዮሐ. 2፥13–14። አንዳንዶች ጌታ ሲሰቀል መጋረጃው ተቀድዷልና አያስፈልግም ይላሉ። ነገር ግን ጌታ ሙቶ ከተነሳና ካረገ በኋላ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድላቸው ድረስ ተግተው ይጸልዩበት ነበር። ሉቃ.25፥53።

አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድላቸው ነው እንጂ ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ዕውቀትን ስለሰጣቸው አልተጠቀሙበትም ይላሉ። ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ እጅግ ተግተው፥ ይጸልዩበት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሥራ.2፥46።

እንዲያውም ሐዋርያት በ9፥በ9 ሰዓት ለጸሎት ሲሄዱ በቤተ መቅደስ ሕሙማንን ይፈውሱ እንደነበር እንረዳለን። ሥራ.3፥1–18።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በቤተ መቅደስ ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ እየወረደለት ተመስጦ እየመጣበት፥ ከጠላት ሁሉ እንዲድን መንፈስ ቅዱስ በዚያ ቤተ መቅደስ መመሪያ ይሰጠው ነበር። ሥራ.22፥17።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በቤተ መቅደሱ የተከለከለ አንድ ዐቢይ ነገር ቢኖር ለኃጢአት ሥርየት ሲባል የእንስሳት ደም ማፍሰሱ (መስዋዕት አሪቱ) ነው። ምክንያቱም 1ኛ ቆሮ.5፥7 ዕብ.10፥10-15 በመሳሰሉት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ ለዓለም ኃጢአት ሲል የዓለም መስዋዕት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰዋልን ነው።

ቤተ መቅደሱንና በውስጡ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት ግን ባርኮ ሰጥቶናል። ባርኮ የሰጠን መሆኑም የሚታወቀው፥ የሆሣዕና ዕለት ቤተ መቅደሱን ሲያጸዳ ያለአግባብ የገቡትን እንስሳትን በጅራፍ እየገረፈ አስወጣ፥ የወርቅና የብሩን መለዋወጫ መደብሩን ገለባበጠ ይላል እንጅ:-

ዕጣኑን ጥንሐውን፥ ማዕጠንቱን፥ መቋሚያውን ከበሮውን፥ መሶበ ወርቁን፥ ጽናጽሉን ሥዕሉን ታቦቱን በአጠቃላይ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያሉትን ንዋያተ ቅዱሳት አውጥቶ ጣለ አይልም። ስለዚህ ሁሉን ነገር በስሜ አድርጉት ስላለ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመን በአዲስ ተፈጥሮ፥ በአዲስ መንፈስ፥ በአዲስ ሕይወት በቅዱስ ስሙ እንጠቀምበታለን።

አንዳንድ ሰዎች ናቡከደናፆር ኢየሩሳሌምን ወርሮ ቤተመቅደሱን ባፈረሰበት ወቅት ጠፍቶ ሳይሆን አይቀርምና ክርስቶስ በመጣበት ወቅት በቤተ መቅደሱ ታቦት አልነበረም ይላሉ። ለእውነተኛ ሰው ግን ይኑርም አይኑርም በእግዚአብሔር ዘንድ በተለይ በሐዲስ ኪዳን የታቦት ክብር በምድር ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ሆኗል። የእግዚአብሔር ታቦት በሰማይ ታየ ይላልና። ራእ.11፥19 ይኸም ደግሞ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ይልቅ በሐዲስ ኪዳን ዘመን የታቦት ክብር እጅግ የበለጠ መሆኑንና በሐዲስ ኪዳን ልንገለገልበት እግዚአብሔረ የፈቀደ መሆኑ ያመለክታል። እግዚአብሔር ባይፈቅድ ኖሮ ክብሩን በሰማይ አያሳይም ነበርና ነው።

በብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሴ አማካይነት ታቦት የተሠራው ከግራር እንጨት ሲሆን፥ ጽላትም የተሠራው ከድንጋይ ነው ብለናል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ማለትም የግራር እንጨትና ድንጋይ በእኛ ዘንድ የቱን ያህል የተናቁ እንደሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ለምሳሌ ያህል አንድን ሰው በስድብ የመጨረሻ ምራሉን ለመጣል ስንፈልግ ድንጋይ ብለን እንሰድበዋለን። ይህም ከፍጥረት ሁሉ ድንጋይን የቱን ያህል እንደምንንቅ ያሳያል።

የግራር እንጨትም እሾሃማ ከመሆኑም በላይ ከእንጨቶች ሁሉ የተናቀ ነው። ለእጅ በትር እንኳ አይሆንም ብዙ ጊዜ ለቤት መሥሪያም አያገለግልም። አንዳንድ ጊዜ በወራቱ ካልተቆረጠ በቀር፥ በአጠቃላይ ከእሱ የሚበልጡ እንደወይራ፥ ጥድ፥ ዝግባ የመሳሰሉት የከበሩ ዛፎች ስላሉ የግራርን እንጨት ከቁጥር የሚያገባው የለም።

እግዚአብሔር ግን እነዚህን የተናቁትን ሁለት ነገሮች ማለትም የግራር እንጨትንና ድንጋይን የክብሩ ዙፋን እንዲሆኑት መርጦ መለኮታዊ ኃይሉን አሳድሮባቸዋል። ለምን ቢባል ታቦቱ፥ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍሏል፥ የኢያሪኮን ግንብ አፍርሷል፥ የፍልስጥኤማውያንን ጣዖት አንኰታኩቷል፥ ደቁሶታል፥ አመድ አድርጐታል፥ ክህነት ሳይኖረው የነካው ዖዛ የተባለውንም ሰው ገድሏል። ልዩ ልዩ ተአምራትን አድርጓል።

በሌላ በኩልም እሥራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ምልክት በመሆኑ እሥራኤልና እግዚአብሔርንም አገናኝቷል።

ይኸም እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ እንደ ማይንቅ ያረጋግጣል። «እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ ይላልና (ዘፍ.1፥31)።

እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ማንኛውንም እጅግ መልካም ነው ብሎ ከመሠከረለት በሰው ዘንድ የተናቀውንም እጅግ የሚያከብር መሆኑን በዚህ ከተረዳን በሐዲስ ኪዳንም ታቦት ከእብነ በረድ ከማይነቅዝ እንጨት ተሠራ ቢባል በአእምሮአችን እነዚህን ነገሮች መናቅ አንችልም። በሐዲስ ኪዳን ታቦት የሚሠራው ከዕብነ በረድ ድንጋይና ከማይነቅዝእንጨት ነው።

አገልግሎቱም የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን ነው። በታቦት ላይ የሚጻፈውም «አልፋ ዖሜጋ» ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው የዘለዓለም አምላክ የሚለው ቅዱስ ስሙ ነው። በታቦቱ ፊት የሚሰግደውም ለዚህ ቅዱስ ስም ነው።

«ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበርከክ ይላልና (ፊልጵ 2፥10) እሥራኤልም በታቦቱ ፊት ስግደት ያቀርቡ ነበር (እያሱ 7፥6)።

በብሉይ ኪዳን ሙሴ በታቦቱ ላይ ይሰማው የነበረው የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ እንጂ እግዚአብሔርን አላየውም በታቦቱም ላይ ሆኖ ሁል ጊዜ ይሰማ የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንንም ወንጌላዊው ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» (ዮሐ.1፥1) ይልና በቁ 14 ላይ ደግሞ ቃልም ሥጋ ሆነ ይላል ይህም ሰው የሆነ አምላክ ኢየሱስ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም ይህ ሥጋዬ ነው ይህም ደሜ ነው ብሎ ሕብስቱንና ወይኑን ሰጥቶናል። ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን ታቦት ማለት ለዓለም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠ የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የክብሩ ዙፋን ነው።

«በላይ በሰማይ በታች በምድር የማናቸውንም ምሳሌና ቅርጽ በፊትህ አታድርግ አትስገድለትም» (ዘጸ. 20፥4–5) የመሳሰሉትን ጥቅሶች በመጥቀስ ታቦት አያስፈልግም የሚሉ አሉ። ይህ ጥቅስ በእግዚአብሔር ፈንታ ለሚመለክ ጣዖት እንጂ የክብሩ መግለጫ ለሆነው ታቦትና እሱ ፈቅዶ ለሰጠን የቅዱሳን ሥዕልና መስቀል የሚጠቀሱ አይደለም። ለማምታታት ካልሆነ በቀር። አንዳንድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተቃዋሚ ክፍሎች ደግሞ የሐዲስ ኪዳንን የታቦት አገልግሎት አጥብቀው ሲቃወሙ ለተቃውሟቸውም መነሻ የሚያደርጓ ቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

1. (ኤር.3፥16)። ላይ ከእንግ ዲህ የእግዚአብሔርን ታቦት ብላችሁ የማትጠሩበት ጊዜ ይመጣል» ስለ ሚል በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ታቦት ብለን መጥራት የለብንም ይላሉ።

እንግዲህ አስቀድሞ በራስ ስሜት ከመተርጐም ይልቅ በመንፈስ ማስተ ዋሉ ይበጃል። ነቢዩ ኤርምያስ ይህን ያለበት ምክንያት፥ እሥራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበትን፥ ጠላትን ድል የሚያደርጉበትን፥ ከእግዚአብሔር በረከትን የሚያገኙበ ትን የቃል ኪዳን ታቦቱን እየተው ወደ አምልኮ ጣዖት ተመለሱ፥ በዚህ ጊዜ ግልጥ አድርጐ ከባቢሎን ናቡከደነፆር ይመጣል ኢየሩሳሎምን ይወራል፥ ቤተ መቅደሱን ያፈርሳል። እናንተ ንም ማርኮ ወስዶ 70 ዓመት ይቀጠ ቅጣችኋል ብሎ ትንቢት ተናገረባቸው ያለውም አልቀረም፤ ናቡከደነፆር መጣ፤ ኢየሩሳሌም ተወረረች፥ ቤተ መቅደሱም ፈረሰ፥ ንዋያተ ቅድሳቱም ተዘረፉ፥ እነሱም ተማርከው ሄዱ፥ አሁን በሰው አገር ጠላትን ድል የሚያደርጉበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት የእግዚአብሔር ታቦት አልተገኘም፥ ያን ጊዜ የነቢዩ ቃል ተፈጸመ። የእግዚአብሔር ታቦት አልተገኘምና የታቦቱን ስም መጥራት አልቻሉም። ይህን ትንቢት ለምን ተናገረ ብለው ኤርምያስን የገዛ ወገኖቹ ከመጸዳጃ ቤት ከተውታል። የተናገረው ግን አንዱም አልቀረም ተፈጸመ፥ እነሱ ቅጣታቸውን አገኙ እንደተባለውም ታቦታቸውን አጡ።

እኛ የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ግን ታቦታችን አልጠፋብንም ምናል ባት የጠፋባቸው ለማያምኑ ነው እንጂ፥ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ለእኛማ ሁላችንም እንድንመለከተው በሰማይ እንዳለ አሳይቶናል። (ዮሐ.ራእ.11፥19)

ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ሥርዓት የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን አድርገን እንጠቀምበታለን። ይህም ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን የማክበራችን ምልክት ነው።

2ኛ. ደግሞ መረጃ የሚያደርጉት (ኤር.31፥31) ላይና (ዕብ.8፥ 2ኛ ቆሮ.3፥2–4) ላይ ያለውን «እነሆ ከእስራኤል ጋር አዲስ ቃል ኪዳን አደርጋለሁ በእነሱም ሕጉን በልቦ ናቸው አኖራለሁ፥ ሕጌንም በልቦና ቸው እጽፋለሁ» የሚለውን ጠቅሰው ሕጉ በልቦናችን ካለ በልቦናችን ከተጻፈ ሕጉ የተጻፈበት ታቦት ምን ይሰራልና የሚል ነው። ይኸም ደግሞ አለማስተዋል ነው። በመንፈስ ላስተዋል ሰው ግን እንደዚህ ነው አምላካችን ሰው ሆኖ ሥጋችንና ነፍሳችንን ተዋሕዶ የእኛን እዳ በደል በመስቀል አስወግዶ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ሲያወጣን እሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወታችን ስለሚኖርና ፍቅሩ ስለሚገዛን ከፍቅሩ የተነሳ ሕጉን መጠበቃችንን ነው የሚያመለክተው «ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው ይላልና» (ሮሜ.13፥10)። በተጨማሪም (ሕዝቅኤል 36፥25–10) እንደሚለው አምነን ስንጠመቅ 2ኛም ስንወለድ አዲስ ልብ፥ አዲስ መንፈስ እናገኛለን።

ይኸም አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ሲኖረን ሕጉን እንድንጠብቅ ያደርገናል። በአጠቃላይ የክርስትና እምነት ማስተዋሉን ሰጥቶን ሕጉን እንድንጠብቅ፥ ኃጢአትን እንድናሸ ንፍ ዕድል ማግኘታችንን ያመለክታል እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሙሉ በእኛ ልቡና ይቀረጻል ማለት አይደለም።

እስኪ አንድ ጥያቄ እንጠይቅ «ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ ሕጌንም በልቡናቸው እጽፈዋለሁ» የሚለው ቃል:- ቃል በቃል በሐዲስ ኪዳን፥ ሕጉን በልቡናችን ብቻ እንጂ ሕጉ የተጻፈበት ሠሌዳ ጽላት ታቦቱም አያስፈልግም ለማለት ከሆነ የእግዚ አብሔርን ሕጉንና ቃሉን ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራእይ ድረስ በቃሉ ይዤአለሁ የሚል አለ ወይ? የለም። እንግዲያስ ሕጉ የተጻፈበት መጽሐፍ ቅዱስ በብራና ቢሆን ኖሮ አህያ የማይችለውን መጽሐፍ ቅዱስ ተሸከ መን የምንዞር ከሆነ፥ እግዚአብሔር ተአምራት ያደረገበትን ቅዱስ ስሙ የተጻፈበትን የሥጋውና የደሙ የክብረ፥ ዙፋን የሆነውን ቅዱስ ሰሌዳ (ታቦት) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የማንጠቀምበት ምክንያት ምን አለ። ለነገሩ ተናገርን እንጂ የሐዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን የተለየ ነው።

ይኸውም 1ኛ/ የሥጋውና የደሙ የክብሩ ዙፋን ሆኖ ሁለተኛ ደግሞ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አልፋ ኦሜጋ የሚለው ቅዱስ ስሙ ስለተጻፈበት ነው። እንጂ ሕጉማ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል። በመ ንፈስ አስተውሎት የክርስቶስ ሥጋና ደም ክብሩ የቱን ያህል እንደሆነ ለሁላችን ግልጥ ነው። ታዲያ ይህ ክቡር ሥጋውና ደሙ በቅዳሴ ጊዜ የት ላይ ከብሮ ይቀመጥ። አባቶች ይህን በመንፈስ አስተውለው ሰው ከመሆኑ ሥጋን ከመልበሱ በፊት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ ጋር ሲነጋገር ዙፋን ያደረገውን ታቦት ተብሎ የተጠራውን እንጠቀም ብለው አባቶቻችን ሲጠቀሙ ቆይተው ለእኛ አስተላልፈዋል። እኛ ያለጥርጥር አክብረን ብንጠቀምበት እንከብራለን እንጂ አንዋረድም። ታቦቱን እንደሆነ እኛ ብንንቀው እግዚአብሔር አይን ቀውም፥ በበለጠም አክብሮታል። ሰማይን ከፍቶ ለዮሐንስ የታቦቱን ክብር ማሳየቱ እኛ የምንንቀውን ታቦት እግዚአብሔር እንዳከበረው መረጃ ነው። (ራእ.11፥19)።

እኛ ክርስቲያኖችም ሁላችን የክርስቶስ ማደሪያዎች ነን (ኤፌ.2፥22። 1ኛ ቆሮ.፥3፥16 1ኛ ቆሮ.6፥19 2ኛ ቆሮ፥6) እንመልከት የእያንዳንዳችን ሕይወት ታቦት የሆነው እንዴት ነው? የሙሴ ታቦት እሾሁ ተመልምሎ ተወግዶ ነው የእግዚአብሄር ማደሪያ (ታቦት) የሆነው በእኛም ላይ የነበረ የኃጢአት እሾህ በደሙ ተመልምሎና ተለቅሞ ተቃጥሏል። ታቦቱ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፈለ፥ እኛም በጥምቀት ማደሪያው ታቦቱ ስንሆን የኃጢአትን ወንዝ ከፍለን ምድረ ርስት ገብተናል። ታቦቱ የኢያሪኮን ግንብ አፍርሷል እኛም የበደላችንን ግንብ በክርስቶስ ደም አፍርሰናልና የክርስቶስ ታቦቶች ለመሆናችን ጥርጥር የለውም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን። ✣

# ኢንጥበብ

## የቦረዳው ድንቅ ዋሻ

በሰሜን ኦሞ በሳቱሳ አውራጃ በቦረዳ ወረዳ ልዩ ስሙ መተቃሜሎ በሚባል ቀበሌ በ1984 ዓ.ም. አንድ ገበሬ በሬዎቹን ጠምዶ ለማረስ ሲል በሬዎቹ ወደ ግራና ቀኝ እየሳቡ አስቸገሩት። የጠመደውን ፈቶ ምናልባት በትክክል ያልጠመዳቸው መስሎት በድጋሚ አስተካክሎ ጠመደ። አሁንም በሬዎቹ ወይ ፍንክች፤ ከዚያማ ዕጹብ ድንቅ የሆነ ክስተት ታየው። ወሬው ከአካባቢው



አቶ ወልደ ገብርኤል ሎሬ

አልፎ ወላይታን አጥለቀለቀ። ከአንድ ሰው አልፎ ከሁለት ሰው ሰማሁት። ነገሩን ለማጣራት ድርጊቱን ያየውን ሰው ፍለጋ ሰሜን ኦሞ ለመሄድ በማሰብ ሳለሁ የእግዚአብሔር ሥራው ድንቅ ነውና የታሪኩን ባለቤት እግዚአብሔር አዲስ አበባ ድረስ አመጣቸው። ነገሩን በማስረጃ ለማስደገፍ ላይ ታች ወጥቼ ወርጄ አንድ ጭብጥ ላይ ደረስኩ። ይህን ዕጹብ ድንቅ ተአምር ሁሉም መስማት አለበት ስላልኩ ከአቶ ወልደ ገብርኤል ጋር ወደአደረግነው ቃለ ምልልስ ላምራችሁ። እናንተም የራሳችሁን ውሳኔ ስጡ።

ጥያቄ – ስምዎ ማን ይባላል?

መልስ – ወልደ ገብርኤል ሎሬ

ጥያቄ – ከወላይታ ክፍለ ሀገር እንደመጡ ሰምቻለሁ ለምን መጡ?

መልስ – ጉዳይ ስላለኝ።

ጥያቄ – በወላይታ ውስጥ ተጋነው የሚወሩ አያሌ ነገሮች አሉ። በተለይም በአንድ ዋሻ ውስጥ ስለተገኙት ጽላቶች፤ ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

መልስ – በመሠረቱ በቦረዳ ወረዳ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ ጽላት እንዳለ የተረጋገጠ ነው።

ጥያቄ – ማን ነው ያረጋገጠው?

መልስ – ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንደሚባል ከመሠረቱ ልነሳልህና በዋሻው ውስጥ ጽላት እንዳለ መላእ ክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጹላቸው ለአራት ልጆች ነበር። እነዚህ ልጆች ለእኔም ያዩትን ነግረውኝ ነበር። በዚያን ጊዜ ግን እኔ ስለሚያወሩት ነገርም ሆነ ስለሃይማኖት ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌለኝ እምነት የለሽ ዱዳ (የሃይማኖት) ነበርኩ ማለት ይቻላል። ስለዚህ ለነገሩኝ ነገር ትኩረትም አልሰጠሁትም፤ በዝምታ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አለፍኩት። እነርሱም ለአካባቢው ሕዝብና ንገሩ ለተባሉት ለአቅራቢያ ቤተክርስቲያን ካህናት ሳይናገሩ ቀሩ።

ለሁለተኛ ጊዜ አቶ ቲና ያሜ የሚባል ሰው ጥምቀት ውሎ ሲመለስ ከዚህ ታምረኛ ዋሻ ውስጥ ብዙ የሚሆኑ መላእክት ሲወጡ ይታየ ዋል። ከእነዚያም እልፍ መላእክት መካከል ሁለቱ ወደ እሱ መጥተው በዋሻው ውስጥ ጽላት እንዳለና በክልሉ ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ካህናት ሄዶ እንዲናገር ሕዝብ እንዲያውቀው እንዲያደርግ ነገሩት። እርሱ ግን ወንድሙ የሌላ እምነት ተከታይና ሰባኪ ስለነበር ነገሩን አጥላላበት። ምትሐት እንደሆነ አሳምኖት ነገሩን አፍኖ እንዲይዘው ስለነገረው ደብቆ ሳይናገር ቀረ። (ለእኔ ግን እዚህ ውስጥ ብዙ ጽላት እንዳለ መላእክት እንደነገሩት ነግሮኛል) በተላከው መሠረት ተልዕኮውን ስላልፈፀመ በአሁኑ ጊዜ አንደበቱን ዘግቶት ለምሥክርነት ይገኛል፤ ሄዶ ማየትም ሆነ መጠየቅ ይቻላል። ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ ለአንዲት ልጅ ይገለጹላትና ሄዳ ለእናትዋ ያየችውን ትነግራታለች። እናትየውም የሌላ እምነት ተከታይ ስለሆነች እዚህ ዋሻ ውስጥ የሚገኘው ሰይጣን ነው ጽላት የሚሉትም ያው ሰይጣን ነው ብላ ማንቋሸሽና ልጅቱም ለማንም እንዳ ትናገር ታስጠንቅቃታለች። በሦስተ ኛው ቀን ሴትየዋ ሞተች።

ሴትየዋ በሞተች ሰሞን ለእኔ ደግሞ ተገለጠልኝ። በተገለጸልኝ ጊዜ ከማለዳው አንድ ሰዓት ነበር። ፀሐይ ወጥታ ነበር። የወጣችው ፀሐይ ከወትሮዋ ባልተለመደ ሁኔታ ጨረ ርዋን ሦስት ቦታ ከፍላ ታየችኝ። ከአጠገቤ የነበረው ሴባ ዶዴ የተባለ ሰውም ይኸን እንግዳ ነገር አይቶ በመደናገጥ ከአጠገቤ እየሮጠ ወደ ቤቱ ሄደ። እኔም እንደ እሱ በሩጫ ለመሄድ ብሞክር አልቻልኩም። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን በሬዎቼን ጠምጄ ላርስ ብዙ ሞክሬ በሬዎቹ ግራና ቀኝ እየሳቡብኝ አስቸግረውኝ አሥሬ ስጠምድ ስፈታ ነበር። እግሬ መንቀሳ ቀስ ተሳነው ሽቅብ ስመለከት ከላይ ድንኳን ተወጥሮ አየሁ። ሁለት መስኮቶች አሉት። ይህን እያየሁ ሳለ ጨረርዋ ሦስት ቦታ ተከፍሎ የነበረው ፀሐይ አንድ ሆነ። ወዲያውም ያ የተወ ጠረው ድንኳን ከዓይኔ ጠፋ። ይህ የሆ ነው ኅዳር 19 ቀን ጠዋት ላይ ነበር።



መላእክት ተገልጠውላቸው በዋሻው ውስጥ ጽላት መኖራቸውን እንዲነግሩ አዝዘዋቸው ትዕዛዙን ባለመፈጸማቸው አንደበታቸው የተዘጋው አቶ ቲና ያምኤ

የጠዋቱ ሁኔታ ምን እንደሆነ ግራ እያጋባኝ እንደ ገና ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት አሁንም በሬዎቼን ጠምጄ ላርስ ስል የጠዋቱ ድንኳን በጠዋቱ ቦታ ላይ ተወጥሮ አየሁት። ከተወጠረው ድንኳን ውስጥም አራት ሰዎች ወጡ። ከአራቱ ሁለቱ ወደ እኔ መጡ። በቀኝ ያለው ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን በግራ በኩል ያለው ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን ከነገሩኝ በኋላ በአፍጢሜ ተደፋሁ። ወዲያው ተነስ ብለውም አጣደፉኝ። እሺ ብዬ ተነሳሁ የምንነግርህን በደንብ አድምጥ ብለው ተናገሩኝ። በዋሻው ውስጥ ጽላት እንዳለና ጽላቶቹም የሚያወ ጣቸው ካህን ካገኙ እንደሚወጡ ነገሩኝና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ለካህናቱ እንድናገር አዘዙኝ።

እኔም በታዘዝኩት መሠረት ሄጄ በአቅራቢያዬ ለሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት ተናገርኩ። እኔንም በቀድሞ ስሜ ሳይሆን ወልደ ገብርኤል ተብዬ እንድ ጠራና እንድጠመቅ መላእክቶቹ ነግረ ውኝ ስለነበር አጥምቁኝ አልኳቸው። ቅዳሴ ካለቀ በኋላ ስለነበር በማግሥቱ




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

እንደምጠመቅ ካህናቱ ነግረውኝ በማግሥቱ ተጠመቅሁ።

ጥያቄ — ቀድሞ አልተጠመቁም ነበር?

መልስ — እንኳን ልጠመቅ ሃይማኖት የለሽ ነበርኩ። አባቴ እንዲያውም ጠንቋይ ነበር። እኔ ግን የአባቴንም አልከተልም ነበር። ወንድሞቼም የሌላ እምነት አማኝ ስለሆኑ እነርሱንም አልቀርባቸውም እንዳው ዝም ብዩ እኖር ነበር፤ እግዚአብሔር እንደፈጠረኝ።



ጽላቱ ያሉበት ዋሻ የውጭ ገጽታ

ጥያቄ — ፊደል ቆጥረዋል?

መልስ — በፍጹም የፊደል ዘሩንም አላውቀውም ነበር።

ጥያቄ — ታዲያ አሁን ትልልቅ የጸሎት መጽሐፍ በግዕዝ በአማርኛም ሲያነቡ አዮታለሁ ማን አስተማርዎት?

መልስ — በዋሻ ውስጥ ያሉ መላእክት ናቸው ያስተማሩኝ (አሁን አማርኛ በመጠኑ መናገር እችላለሁ። ግዕዝ ማንበብም)።

ጥያቄ — ወደ ዋሻው ይዘዎት የገባው ማን ነው?

መልስ — መላእክቶቹ ናቸው እየመሩ ያስገቡኝ።

ጥያቄ — በዋሻው ውስጥ ያዩት አስደናቂ ነገር ምንድን ነው?

መልስ — በዋሻው ውስጥ ከአንድ ቋጥኝ ውስጥ የመድኃኔ ዓለም፣ የሚካኤል፣ የገብርኤል፣ የኪዳነ ምሕረት፣ የሥላሴ፣ የአቦ፣ የጊዮርጊስ... ሌሎችም ጽላቶች እንዳሉ አይቻለሁ።

ጥያቄ — እርስዎ ካህን አይደሉም፣ ጽላት መሆናቸውን እንዴት አወቁ? ደግሞስ የእያንዳንዱን ጽላት ለይተው እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?

መልስ — (ፈገግ ብለው) እግዚአብሔር ሁሉንም መግለጽ ይችላል። ይህን ሁሉ ለእኔ የነገሩት መላእክቶቹ ናቸው።

ጥያቄ — የጽላቶቹ አቀማመጥ እንዴት ነው?

መልስ — ባንድ ቋጥኝ ውስጥ እንደተደረደረ ዕቃ ዙሪያውን ሠልፍ ሰርተው ነው የተቀመጡት ከእነርሱም በወርቅ፣ በብር የተለበጡ አሉባቸው።

ጥያቄ — ወደ ዋሻው ውስጥ በገቡ ጊዜ ጽላቶቹን በእጅዎት ነክተዋቸዋል?

መልስ — እነርሱ ፈቅደውልኝና አዘውኝ የገብርኤልን ጽላት ከነበረበት ቦታ አንስቼ ሌላ ቦታ እንዳስቀምጥ ታዝዤ አንስቼ ያሳዩኝ ቦታ አስቀምጫለሁ። ትንሽ ቆይተውም ወደ ቀድሞው ቦታ እንድመልስ አዘውኝ ወደ ቀድሞው ሥፍራ መልሻለሁ። በእውነቱ ለመናገር ጽላቱ በይዘቱ በጣም መጠነኛና ቀላል መስሎ ሲታይ ነገር ግን አዘውኝ ባነሣሁበት ጊዜ ኩንታል ጤፍ መሸከም ይቀላል። እንደውም ባነሳሁበትና በታዘዝኩበት ስፍራ ባስቀመጥኩ ጊዜ አይኔ ሁሉ አብጦ ነበር።

ጥያቄ — ጽላቱን በነኩ ጊዜ ምንም ዓይነት ስሜት አልተሰማዎትም?

መልስ — እኔ በመላእክቱ ትዕዛዝ ስለሆነ ጉዳት አልደረሰብኝም ነገር ግን ሌሎች ገብተው ያዩት ሰዎች እንደ እሳት እንደሚፋጁና እንደሚያቃጥሉ መንካትም እንደማይቻል ተናግረዋል።

ጥያቄ — የከልሉ ጳጳስ ወደ ዋሻው ገብተው የተባሉትን ጽላቶች አይተዋል?

መልስ — ከእኔ ጋር አብረው ወደ ዋሻው ገብተው ጽላት መኖሩን አየተው ወጥተዋል። እንዲያውም በዙሪያው ለተሰበሰበው ሕዝብ የቦታውን ታላቅነት ከሌሎቹ በሀገራችን ከሚገኙ ቅዱሳን ቦታዎች ጋር አስተካክለው በመናገር በዋሻውም ውስጥ ጽላት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ማየታቸውን አረጋግጠዋል። በአጠገቡ ያለውንም የጸበል ቦታ ባርከው አካባቢውም እንዳይታረስ በክብር እንዲጠበቅ በመላከቶቹ ባሳዩን ቦታዎችም ላይ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አዘው ነው የሄዱት። ነገር ግን በዓይናቸው ያዩትን በጆሩዋቸው የሰሙትን ነገር በልቦናቸው ለብቻቸው አፍነው መያዛቸው እስከ አሁን ድረስ ሊገባኝ ያልቻለ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል። በአካባቢው የሚደረገው ተአምር እውነተኛና ሕዝብ ያወቀው የተለያዩ **ማርያምን ከማያምኑት የሌላ እምነት** አባላት የነበሩት እንኳን በሁኔታው አምነው እየተጠመቁ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አባል (ተከታይ) እየሆኑ እየታየ ለምን እንደሚደበቅ ግራ ያጋባኝ ነገር ነው። ነገር ግን እኔ እስከ ሞቴ ድረስ የእግዚአብሔርን ኃይል እመሰክራለሁ።

ጥያቄ – በአካባቢው ብዙ ተአምር እየተፈፀመ ነው ማለት ነው?

መልስ – በግልጽ እንጂ ከብዙዎቹ አንዳንዶቹን ብጠቅስልህ። የሌላ እምነት ማለቴ የሚሽን እምነት ተከታይ የነበረ ሰው ማርያም ራስዋ ተገልጻ እንደታየችው ገልጾልኛል። ይህ ሰው ራሱ ሲመሰክር «እኔ **የሌላ እምነት** አማኝ ስሆን የማምነው በእግዚአብሔር ብቻ ነው የማርያምን አማላጅነት አላምንም ነበር። ነገር ግን በማርስበት ቦታ ማርያም ወደ ምሥራቅ ፊትዋን አዙራ ቆማ መጽሐፍ ይዛ ስትፀልይ አይቻለሁ። በጸጉርዋ ላይ ፀሐይ የተጠመጠመ ይመስላል። አንተ ብትተወኝም እኔ ግን አልተውኩህም» አለችኝ ብሎ ተናግሯል። ይህንን ደግሞ ራሳቸው ጳጳሱ ባሉበት የመሰከረው ነው። ይህ ሰው ዋሻው ያለበትን ቦታ በይዞታ የሚያርስ ስለነበር ጳጳሱ በአካባቢው ማንም ሰው እንዳያርስ ብለው ያስተላለፉትን ማስጠንቀቂያ ጥሶ «ታዲያ ምን ልብላ» ብሎ አርሶ በቆሎ ይዘራበት ጀመር።

እኔም ይህን ሲያደርግ ስለደረስኩና አባታችን አትረስ ብለው እያስጠነቀቁህ አንተ ለምን አረስክ ብዬ ተቆጣሁት። እርሱም እባክህ እዚህ ቦታ ያለው ሠይጣን ነው ብሎኝ ቁጣዬን ከምንም ሳይቆጥረው ሥራውን ቀጠለ። ለአንድ ተልዕኮ አርባ ምንጭ ደርሼ ስመለስ ወደ ዋሻው ገብቼ እጣንና ሰንደል እያጠንኩ እግዚአብሔርን በሰላም አድርሶ በሰላም ስለመለሰኝ አመስግኜ ስወጣ አሁንም ያርሳል አንተ ሰው አትረስ ብዬ ብነግርህ እምቢ አልክ አይደለም ብዬ ወደ ቤቴ ሄድኩ። ወዲያው ከባድ ዝናብ ዘነበ ሰውየውም ስራውን አቁሞ በሬዎቹን ፈቶ ወደ ቤት ሄደ። ወዲያውም በሬዎቹ ሞቱ። አሁንም «ያዲያቆነ ሠይጣን ሳያቀስ አይቀርም» እንደሚሉት በእጄ እቆፍራለሁ ብሎ በዶማ ሲቆፍር ያላሰበው ያልጠበቀው መቅሰፍት ደረሰበት። እራሱን ስቶ ወደቀ ወገቡም ተበጥሶ የአልጋ ቁራኛ ሆነ። አልጋውም ላይ ሆኖ ይኼ ነገር የሆነብኝ ወልደ ገብርኤል ሲያስጠነቅቀኝ እምቢ ብዬ ነው ብሎ ምናልባት እግዚአብሔር ቢምረኝ ብሎ በዋሻው አጠገብ ካለው ፀበል እንድታመጣለት የ7 ዓመት ልጁን ላከ። እርሷም ጀሪካን ይዛ ፀበሉ ጋር ደርሳ ፀበሉን ለመቅዳት ጀሪካኑን ወደ ፀበሉ ስትጠልቅ ወደ ላይ አንስቶ ከመሬት ጣላት፤ ራስዋንም ስታ ወደቀች። ሰዎችም ተጠራርተው መጥተው አፋፍ ሰው ወሰዷት። ሌላኛው ልጁ ደግሞ ከዛፍ ላይ ወድቆ ክፉኛ ተጋጋጠ። ቤተሰቡ ሁሉ የቃለ ሕይወት አማኝ ነበሩ። አሁን ሁኔታውን ካዩና ከመረመሩ በኋላ የደረሰባቸው መከራ ትምህርት ሆኑአቸው ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተመልሰው ተጠምቀው የታመሙትም ድነው አሁን ይገኛሉ።

ሌላው ደግሞ ይህ ሁሉ ተአምር ለሚደረግበት ቦታ ካህን መላክ እንዳለበት ለክልላችን ጳጳስ ለብፁዑ አቡነ ዘካርያስ አስታውቀን አባታችንም አንድ መነኩሴ ላኩልን። መነኩሴው ግን እዚያ ቦታ ሊቆዩ አልቻሉም። ለተወሰነ ቀን እየተለማመጥን ከቆዩ በኋላ ትተው ሄዱ። የአካባቢውም ሕዝብ እጅግ በጣም አዝኖ በቃ የመጡትም መነኩሴ ሄዱ እነዚህን ሁሉ በሽተኞች ማን ያጥምቅ ከሌላ እምነት የሚመለሱትንስ ማን ያጥምቅ እያሉ ሲቸገሩ። እኔ በዋሻው ውስጥ ያሉ መላእክት ከወደዚህ አካባቢ የሚመጡት መነኮሳት ለዚህ ቦታ የሚስማሙ አይደሉም እኛ ራሳችን ለቦታው የሚስማማ መነኩሴ እናመጣለን ብለውኛልና አትዘኑ አሁን እንዲያውም እየመጡ ነው ብዬ አጽናናኋቸው። ከጥቂት ቀን በኋላ አንድ ባህታዊ መነኩሴ ወደዚያ ዋሻ መጡ። ከየት እንደመጡም ሲጠይቁአቸው በጫካ ውስጥ የሚኖሩ እንደነበሩ ተናገሩ ማን ወደዚህ ቦታ ላከወት ተብለው ሲጠየቁ ዓይናቸውን ወደ ሰማይ ሰቀል አድርገው እግዚአብሔር ነው ብለው ሁላችንም ደስ አለን። እግዚአብሔር ስለተስፋው ቃል አይዘገይም አሁንም ሁለቱን እየጠበቅን ነው መላእክቱ ይመጣሉ ብለውኛል።

ጥያቄ – ከዋሻው ውስጥ የቅዳሴ ድምጽ ይሰማል ይባላል ለመሆኑ በዋሻው ውስጥ ሥርዓተ ቅዳሴ ይካሄዳል ወይ?

መልስ – ግሩም የሆነ ሥርዓተ ቅዳሴ በዋሻው ውስጥ አይቻለሁ። ቅዳሴው የሚቀደሰው ደግሞ እንደ እኛ ዓይነት በሆኑ ሰዎች አይደለም። የሚቀድሱት ስድስት ክንፍ ያላቸው መላእክትና ግንባራቸው የእግርና የእጃቸው ጥፍር ብቻ የሚታይ ሰውነታቸው እንደ ዝንጀሮ በፀጉር በተሸፈነ ሰዎች ነው። ባለስድስት ክንፍ መላእክትም አሉ። ከመቶ ያላነሱ ሁለት ክንፍ ያላቸው ህፃናትም በዋሻው ውስጥ አሉ። ሽማግሌዎቹ ይቀድሳሉ፤ ሁለት ክንፍ ያላቸው



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ህፃናት ፀናጽል መስቀል ይዘው ያሸበሸባሉ ይዘምራሉ። ስድስት ክንፍ ያላቸው ከበሮ ይዘው ይመታሉ። ሌሎች መላእክት ደግሞ ጽላቶቹ አጠገብ ተቀምጠው በደስታ ተውጠው ይታያሉ።

ጥያቄ – ቅዳሴው በምን ቋንቋ ነው?

መልስ – እኔ ብዙም የግዕዝ ቋንቋ ባላውቅም በግዕዝ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። የሚሉት ምን እንደሆነ ለማወቅ ግን በአካባቢው ላሉ ሰዎች ለህፃኑ ሳይቀር የቅዳሴው ድምፅ ስለሚሰማ በአካባቢው ያሉት ዲያቆናት የቅዳሴው ዓይነት ጠይቆ ማወቅ ይቻላል። የአሁኑም ባህታዊ መነኩሴም ያውቀታል።

ጥያቄ – የቅዳሴው ድምፅ በአካባቢው ላለ ሰው ሁሉ ይሰማል ማለት ነው?

መልስ – በውስጥ ያለውን ሥርዓት የማየው እኔ ብቻ ብሆንም ቅዳሴውን ግን የማይሰማ ፍጥረት የለም።

ጥያቄ – የቅዳሴው ሥርዓት ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጋር ሲያነጻጽሩት እንዴት ነው? የመናፍቃንንስ ይመስላል?

መልስ – የኦርቶዶክስ ነው። ሲጀምሩ «ተዘከረነ እግዚኦ» ሲሉ እሰማለሁ። እንዲያውም መላእክቶቹ እንደነገሩኝ «በየቦታው ዞረህ አንዲት ሃይማኖት ብቻ እንዳለች መስክር እርሷም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነች። ከእርሷዋ ውጪ ያሉት ለወደፊት አይኖሩም» ብለውኛል። ስለዚህ እኔም የማምንባት በእርሷ ነው፤ የምመሰክረውም ለእርሷ ነው።

ጥያቄ – በዋሻው ውስጥ ያሉት መላእክት ለአካባቢው ሕዝብ ታይተው ያውቃሉ?

መልስ – መስከረም 7 1985 ዓ.ም. መላእክት ከዋሻው ወጥተው ነበር። ብዙ መላእክት የእሳት ነበልባል ይዘው ይመሩአቸው የነበሩት ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ነበሩ። የአካባቢውም ሕዝብ ወየው በእሳት ልንጠፋ ነው ምን መዓት መጣብን እያሉ ተሸብረው ነበር። እኔ ግን አይዙአችሁ መላእክት ናቸው እንደ ሮኬት እየተወረወረ በሰማዩ ላይ የምታዩት እሳት ሳይሆን የመላእክቱ ሰይፍ ነው፤ ከመላእክቱ ሰይፍ ጫፍ ላይ የሚንበለበል እሳት ነበር። የመላእክቱም ሰይፍ እየተምዘገዘገ ወደ መናፍቃኑ ቤት ውስጥ እየገባ ከቤታቸው አስወጥቶ አባሩአቸዋል። መሰብሰቢያ አዳራሻቸው ውስጥ ገብቶ ሁሉ አስወጥቷአቸዋል። ከዛን ጊዜ ጀምሮ መናፍቃን እዚያ ቦታ አይሰበሰቡም። ሴባዶዴ የተባለውም በዛን ወቅት ነበር ወገቡ የተበጠሰውና አሁንም በቤቱ ተኝቶ የሚገኘው።

አይቻለሁ። ከራስዋ በላይ በአየር ላይ ዜር ክብ የሠራ ነገር አለ። አፈጣጠርዋ ከፈረንጅ የሚበልጥ እጅግ ደስ የሚል ነው። የእርስዋ ክብር ከባድ እንደሆነም ላውቅ ችያለሁ። ሁል ጊዜ ለሰዎች ምሕረትን እንዲያገኙ ከመፀለይ አቋርጣ አታውቅም።

ጥያቄ – ሌሎችንስ አላየህም?

መልስ – ሥላሴን አይቻለሁ። ከዋሻ ሲወጡ ሦስት ነበሩ። ወደ ዋሻ ሲገቡ አንድ ይሆናሉ። እነዚህ እነማን ናቸው ስል ሥላሴ መሆናቸውን ነገሩኝ።

ጥያቄ – ወደ ዋሻው ውስጥ ማንም ሰው መግባት ይችላል?

መልስ – ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንም በድፍረት ቢገባ መቅሰፍት ይጠብቀዋል። አንድ የተደረገውን ተአምር ልንገርህ።



ጽላቱ ያሉበት ዋሻ የመግቢያ በር

ጥያቄ – መላእክትን ብቻ ነው ከዋሻው ውስጥ ያየኸው?

መልስ – እመቤታችንን በዋሻው መሐከል መጽሐፍ ቅዱስ ይዛ ስታነብ

አንድ እሑድ ዕለት ከሌሊቱ 11 ሰዓት አንድ ታከለ የሚባል ማሳ ከሚባለው ክልል የመጣ ነው ዋሻው ውስጥ የሚደረገውን ቅዳሴ ሰምቶ ከከተማ ሰው መጥቶ ሁሉም ዋሻው



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ውስጥ ገብቶ ቅዳሴ የሚያስቀድስ መስሎት እርሱም ዘው ብሎ ወደ ዋሻው ውስጥ ገባ። ወዲያው ከዋሻ ውስጥ የሆነ ነገር በጥፊ መትቶ ዘረረው። እኛም በኋላ ከዋሻው ደጃፍ አውጥተን ሊሞት እያጣጣረ ስለ ነበር ወደ እግዚአብሔር ስንፀልይ፥ ፀበሉንም ስናጠጣው በሦስተኛው ቀን ፍጹም ሊድን ችሏል።

ጥያቄ – አሁን ቤተ ክርስቲያን እየተሠራ ነው?

መልስ – ለጊዜው ጽላቶቹ የሚያርፉበት ማረፊያ እየተሠራ ነው።

ጽላቱ አለበት የተባለውን የዋሻውን ቦታ በይዞታነት የያዙትና ብዙ ጊዜ አካባቢውን ካላረስኩ ብለው ያስቸገሩት ኋላ ግን በተአምረ እግዚአብሔር ተስበው ቦታውን ለቤተክርስቲያን ማሠሪያ ከሰጡት ሰው ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌ ነበር።

ጥያቄ – ስምዎት ማን ይባላል?

መልስ – ሃታ ጭላሉ።

ጥያቄ – አቶ ሃታ በዚህ አካባቢ ነው የሚኖሩት?

መልስ – አዎን የዚህ ክልል ነዋሪ ነኝ።

ጥያቄ – መጀመሪያ የምን እምነት ተከታይ ነበሩ?

መልስ – ማርያምን ከማያምኑት

ጥያቄ – በ ቅድስት ድንግል ማርያምን ከማያምኑት ) እምነት በነበሩበት ጊዜ በዚህ ዋሻ አካባቢ ያዩት ምን ዓይነት ታምር ነበር?

መልስ – ባለፈው ዓመት እኔ ሌላ እምነት አማኝ እያለሁ በታኅሣሥ ወር ላይ ነው ማርያም ተገልጻ ታየችኝ።

ጥያቄ – በየትኛው አካባቢ ነው የታየችዎት?

መልስ – በስተምሥራቅ በኩል ነው።

ጥያቄ – እዚህ ዋሻው አካባቢ ነው?

መልስ – አዎን ዋሻው ጋር ነው።

ጥያቄ – በምን አይነት ሁኔታ ነበር የታየችዎት?

መልስ – እግርዋ ድረስ የሚደርስ ቀሚስ ለብሳለች ጃንጥላም ይዛለች ጽላትም የተሸከመች ይመስለኛል እና እኔም ክብር ይገባሻል ብዬ (እያልኩ) ስማልዳት ከዚያ በኋላ ወደታች ዝቅ ዝቅ እያለች ከፊቴ ተሰወረች።

ጥያቄ – ይህን የተመለከቱት መቼ ነው?



አቶ ሐታ ጭላሉ

መልስ – ጥር 1984 ዓ.ም. ነው።

ጥያቄ – በአሁን ጊዜ በቀድሞው እምነትዎ ጸንተው ነው ያሉት ወይስ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምነት ተጠምቀዋል?

መልስ – ቅድስት ድንግል ማርያምን ካየሁ በኋላ እንኳን በመናፍቃን እምነት ለመጽናት ሞክሬ ነበር ነገር ግን በዚህ ሐሳቤ እስከ መጨረሻው ልጸና አልቻልኩም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አምኜ ላለመጠመቅ ብዙ አስቸግሬአለሁ። ብዙም ችግር ደርሶብኛል።

ጥያቄ – አሁን በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አምነው ተጠምቀዋል ማለት ነው?

መልስ – አዎን።

ጥያቄ – በምን ምክንያት የቀድሞውን እምነትዎን ትተው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አምነው ሊጠመቁ ቻሉ።

መልስ – በመጀመሪያማ ማርያም ተገልጻ አነጋግራኝ በዚህ ዋሻ አካባቢም ብዙ ተአምራት እየተሠራ እያየሁ እኔ ግን በሌላ እምነት ትአማኝነቴ ለመጽናት ወስኜ ነበር ብዙም አስቸግሬ ነበር። ነገር ግን የገብርኤል ዕለት ብዙ ችግር ስፈጥር ሳለ ራሱ መልአኩ ቀሰፈኝ በዚያም ምክንያት ደም አስታወከኝ በጣምም ታመምኩ ቤተሰቦቼም ያልወሰዱኝ ቦታ የለም። ለሞት በተቃረብኩኝ ጊዜ ራሳቸው መላእክቶቹ ሚካኤልና ገብርኤል መጥተው እኛ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነን እኛ ነን ወደ እግዚአብሔር የምናቀርብህ ስለዚህ በእኛ ተራዳኢነት ማመን አለብህ አሉኝ።

ይህ ሁሉ ደርሶብህ ትምህርት ሆኖህ በኛ አማላጅነት አምነህ ይቅርታ አትጠይቅም አሉኝ በተጨማሪም አሁን አንተ የምታምነው እምነት ትክክል አይደለም አሉኝ። እኔም ወደ እግዚአብሔር ጸለይኩ።

«እኔ የማምነው እምነት ምንድን ነው? እኔ እማምነው እግዚአብሔርን አይደለም ወይ? ታዲያ ይኼ ለምን ደረሰብኝ ብዬ እግዚአብሔርን አልቅሼ ጠየቅኩ እግዚአብሔርም መልስ ሰጠኝ በእርግጥ የምታምነው በእኔ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ነው ነገር ግን እነርሱ የእኔ አገልጋዮች ናቸው ስለዚህ በእነርሱም አማላጅነት ማመን ይገባሃል። እንደዚህ ሆነህ ትሞታለህ ወይስ እነርሱን ይቅርታ ትጠይቃለህ አለኝ። ከዚያም ለመዳን ከፈለግህ አንተም ቤተሰብህም መጠመቅ አለባችሁ አለኝ እኔም ከእግዚአብሔር ይኼን መልስ ካገኘሁ በኋላ የነበርኩበት እምነት ወደ ስህተት እንደመራኝ አውቄ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አምኜ በመጠመቅ እኔም መላው ቤተሰቤም ተፈውሰን አሁን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ሆነናል።

ጥያቄ – እግዚአብሔርን ስለ እምነትህ ትክክለኛነት በጠየቅከው ጊዜ በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር መልሱን የሰጠህ?

መልስ – ሔታ አለኝ እኔም ስሜን እንዴት አውቆ ጠራኝ ብዬ በመገረም ማነህ አንተ እኔን የምትጠራኝ ብዬ ስጠይቀው እኔ እግዚአብሔር ነኝ አለኝ እኔ ሳየው (እጃቸውን ዘርግተው በማሳየት) እንደዚህ ግዙፍ ነው። ደግሞም ጐረቤቴ ያለው ገለታ የሚባል ሰው ሁል ጊዜ ጠዋትና ማታ እዚህ ዋሻ መጥቶ እንዲጸልይ ንገረው እምቢ ካለ የእሱ ችግር ነው ብለው ስለነገሩኝ ለሰውየው ነግሬው እሱም ሳያመነታ መልአክቱ ያሉትን ሰምቶ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አምኖ ተጠምቋል።


አዘጋጁ – የቦረዳው ታሪክ በዚህ ብቻ የሚቋጭ አይደለም። ሐመር ይህንን ሁኔታ እስከ መጨረሻው ተከታትላ ለማውጣት ዝግጁ መሆኑዋን በመግለጽ በሚቀጥለው መጽሔታችን ላይ የክልሉ ጳጳስ አቡነ ዘካርያስ የሰጡኙን የቃል ምሥክርነትና ሌሎች የአካባቢው ሰዎች በተለይም የወረዳው ፀሐፊ የሰጡንን የምስክርነት ቃል እናቀርብላችኋለን፤ እግዚአብሔር የዚያ ሰው ይበለን። ✣

# ወላዲተ አምላክ

ከዲ. ደምለው ይነሱ

ንጽሕት ወብርህት ስብሕት ወቡርክት፥
ፀዋሪተ እሳት እሳተ መለኮት።
ሰማይና ምድር የማይችሉትን የቻልሽ፥
ዕፀ ጳጦስ ለምለሟ እንጨት እሳቱ ሳያቃጥልሽ፥
ልምላሜሽ ሳይጠወልግ ሙሴ በደብረ ሲና ያየሽ።
ድንግል በሁለት ድንግል በሥጋ ወድንግል በኅሊና
መሶበ ወርቅ እንተመና፥
የሕይወት እንጀራን የያዝሽ፥
ለሰው ልጆች የሕይወት ምግብ መገኛ ምንጭ የሆንሽ፥
አምላክ በጥበቡ የተጠበበብሽ ያስዋበሽ፥
እድፍ ጉድፍ የሌለብሽ የልዑል ኃይል የፀለለሽ፥
የሕይወት ወይንን የተሞላሽ፥

ቅድስት ድንግል ማርያም
ምስለ ፍቁር ወልዳ




መሰቦ ወርቅ አንች ነሽ ንጽህት የወርቅ ጽዋ አንች ነሽ።
ዕፁብ ድንቅ ነገር መድምም ወመንክር፥
የተዋሕዶ መግለጫ የቃል ሥጋ ሆነ ምሥጢር፥
መትህተ ፈጣሪ ክቡር መልዕልተ ኩሉ ፍጡር፥
መወጣጫዋ መሰላል ማዕከል ሰማይ ወምድር።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የእሳተ መለኮት ማረፊያው የንዳይ መከሊተ ወርቁ፥
ራቁቱንም ቢሆን መንገድ ቢጓዝ በሩቁ፥
በጣም አይዘን ይጽናና ይቆጠብ ከመጨነቁ፥
ወላዲተ አምላክ በቅርቡ አለችለትና ስንቁ።

የነቢዩ ኤልያስ ደመና የአሮን በትር የተባልሽ፥
ለፍጥረታት በሙሉ ለተንቀሳቃሽ ኢ ተንቀሳቃሽ፥
የቀን ሐሩር ገርፎሽ የሌሊት ቁር አኮማትሮሽ፥
ተራሮችን ወጥተሽ ወርደሽ በዓለም ዙሪያ ተንከራትተሽ፥
የሕይወት ዝናምን ተሸክመሽ እቅፍ ድግፍ አድርገሽ
የድህነት ጥም ማሪኪያ ማይነጥፍ የዘለዓለም ደስታ ፈሳሽ፥
የወደቀውን ያነሳሽ የጠፉ ስሙን ያስፋቅሽ፥
መልካም ስምን አሰይመሽ በወርቅ ቀለም ያሳጻፍሽ፥
ርጉም የተባለውን አዳምን ርግምት የተባለችውን ሔዋን
ቡሩክ አዳም ቡርክት ሔዋን ያሰኘሽ
ወላዲተ አምላክ አንች እኮ ነሽ እመ ብርሃን አንቺ እኮ ነሽ

የደመናን ምሥጢር ብናያት ብናሰላስል ብንመረምራት፥
ረቂቅ ናት ድብቅ ናት ከዝናብ ጋር ተጋብሮ አላት
ደመና ከሌለ ዝናም የለ ዝናም ከሌለ ሕይወት የለ፥
ብንጠብቀው እኮ አይመጣም ይቀራል እንደዋለ፥

ዝናም ከሌለ እንደርቃለን፤ እንዳልነበርን እንሆናለን፥
ግብስብስ ገለባ የደረቀ እንጨት ተብለን፥
ማገዶ እንሆን ዘንድ ከነደደ እሳት እንጣላለን።

በመሶበ ወርቅ ብናጤናት ከልብ ብናስተውላት፥
የሥጋ የነፍስ መዳኛ የዓለም ሁሉ ሕይወት፥
የተቀደሰ ሕብስተ መናን ሰማያዊ እንጀራን የያዘች ናት፥
ታዲያ ይህችን መሶበ ወርቅ አታስፈልግም ብንላት፥
ገፍትረን ብንጥላት፥
ሕብስተ መናው በውስጧ ያለው ይበጀናል ያልነው ለድህነት፥
የለም አልተገፈተረም አብሮ አልተጣለም ማለት፥
ውሸት መላ ውሸት የማትስተባበል ውሸት።
ያለምንም ጥርጥር አብሮ ተናቀ፤ አያስፈልግም ተባለ፥
መድኃኒት ተገፈተረ ተወረወረ ተጣለ።

የሕይወት መጠጡን ወይኑን ወድደን የወርቅ ጽዋን ብንንቅ፥
ሊሆን አይችልም እኮ ታይቶም ተደርጐም አያውቅ፥
ለመረመረው ላየው ሰው ምንኛ ያስገርም ያስቅ፥
በውስጡ ያለውን ፈልጐ በመያዣው በመሰብሰቢያው መሳለቅ፥

ወይን በወርቅ ጽዋ ሕብስተ መና በመሶብ፥
ነው እንጅ ያየነ የሰማን ሊበላ ሊጠጣ ሲቀርብ።

እስኪ ወጣት ምን ተሻለኝ? ምን ተሻለህ?
ደመናን ባልፈልግ ባትፈልግ ዝናም በመቅረቱ እደርቃለሁ ትደርቃለህ፥
መሶብን ብገፈትር ብትገፈትር፤ እንጀራው በምን ሊቀርብልኝ? ሊቀርብልህ፥
ስንኳንስ አምላካችን የፈጠረኝ የፈጠረህ፤ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣኝ ያመጣህ፥
በሰው ልማድም ትነወራለህ፥
መሶብ ረጋጭ ጋጠ ወጥ ወንጀለኛ ትባላለህ፥
ጽዋዋን ከወረወርኩ ከወረወርህ ከናቅኋት ከናቅህ፥
የሕይወት ወይኑን በምን ልጠጣ? አንተስ በምን ትጠጣዋለህ?
ታዲያ ወጣት ምን ተሻለኝ ምን ተሻለህ?
ያለመሶብ እንጀራ ያለእናት ኢየሱሴ፥
ያልተጻፈ በሕገ ወንጌል ወይም በኦሪተ ሙሴ፥
ምንም ጥቅም የሌለው እንዳይሆን ከንቱ ውዳሴ፥
እንዳልባል እንዳትባል የበግ ለምድ የለበስ ተኩላ መነኩሴ፥

ስለዚህ ወጣት ስለዚህ...
ያለእናት ኢየሱሴ ማለትህን መዘላበድህን ትተህ፥
ወለም ዘለም ሳትል በትክክል ተገንዝበህ፥
ሰጥ ለጥ ፀጥ ቀጥ ብለህ፥
ድንግልን ወላዲተ አምላክን እመቤቴን እመቤትህን ጋሻ መከታ አድርገህ፥
አመስግናት አወድሳት የፀጋ ስግደትም ስገድላት ናትና አማላጅህ፥
መወጣጫ መሰላልህ መሸጋገሪያ ድልድይህ፥
ከታች ወደላይ የምታወጣህ ከእሳት ባህር የምታሻግርህ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ለወላዲተ አምላክ እመ አምላክ
ይስግድ ወያስተብርክ ኵሉ ብርክ፥
በትንብልናሃ ይእመን ይስበክ ወያስምክ፥
ይበል ሰዓሊለነ ቅድስት በበነግህ ወበበሠርክ፥
እስመ ይእቲ ድንግል በክልኤ ወወላዲተ አምላክ።

ርኅርኅተ ልብ ድንግል መዝገበ ፍስሐ ወተድላ፥
ንጽሕተ ሥጋ ወነፍስ ሰባሪተ መርገም አሸክላ፥
ሰይጣን የዘራው አሜኬላ የዚህች መናጢ ዓለም ሽንገላ፥

እንዳያታልለን እንዳይጥለን እንዳይዘፍቀን ወደመከራ፥
ወዲህ ወዲያ ስንል ስንዋትት በማያዛልቅ ከንቱ ሥራ፥
ስንዘንጥ ስንሽቀረቀር ያለአቅማችን ስንኮራ፥
የዓለም ምኞት፥ የገንዘብ ፍቅር ሲያቃጥለን የተንኮል ዘርን ስንዘራ፥
የባጥ የቆጡን ስንለፈልፍ የመሸ ነጋውን ስናወራ፥
የሰጠንን ሰው ስናወድሰው ስናሞጋግሰው በጕራ፥
ያልሰጠንን ስንቦጭቀው በልሳነ ሐሜት ቆንጨራ፥
በንስሐ ውኃ ሳንታጠብ ቆሻሻችንን ሳናጠራ፥
የመጨረሻዋ ቀን ደርሳ ሳናስበው እንዳንጠራ፥
አለሽና ደግ አንጀት ያውም ለውሻ የሚራራ፥
የመጨረሻዋ ቀን ደርሳ ሳናስበው እንዳንጠራ
እመ ብዙኃን እመ ብርሃን ወላዲተ አምላክ አደራ፥
እመ ብዙኃን እመ ብርሃን ወላዲተ አምላክ አደራ፥
እመ ብዙኃን እመ ብርሃን ወላዲተ አምላክ አደራ። ✣

ለእያንዳንዱ ሰው:-

- ኢዮባዊ ትዕግሥት፥
- አብርሃማዊ ሒሩት፥
- ይሥሐቃዊ ፈቃደኛነት፥
- ያዕቆባዊ ቅን አገልግሎት፥
- ዮሴፋዊ ኀዳጌ በቀልነት
- ሙሴያዊ ለወገን ተቆርቋሪነት፥

በጠቅላላው ደግሞ–

ክርስቲያናዊ ትሩፋት ይኖረው ዘንድ አስፈላጊ ነው።

እርስዎስ ከእነዚህ ስንቱን አሟልተዋል?

ሥነ–ምግባር

# እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

ከዲ. ተክለፃድቅ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ምሳሌዎች፥ ትንቢቶችና ድርጊቶች እየተነገረችና እየተገለጠች ቆይታ እግዚአብሔር የወሰነው ዘመን ሲደርስ ከአባቷ ከኢያቄምና ከእናቷ ከሐና ተወልዳ በአካል ተገልጣለች። ይህንኑ የወላዲተ አምላክን ነገር የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ከቅዱስ መጽሐፍ መጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻው በመዘለቅ የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሷ የሚናገረውን በጥበበ መንፈስ ቅዱስ በመመርመርና ምሥጢሩን በመግለጥ በሰፊው ያስተምሩናል። በዚሁ መሠረትም ከዚህ የአበው በረከተ ትምህርት ለአንባብያን ማቅረብ የሚገባ መሆኑን በማመን እግዚአብሔር እንደፈቀደ በየእትሙ እነሆ ለማለት አሰበናል።

ኦሪት ዘፍጥረት 7፥2–23

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለጻድቁ ኖህ የተፃፈውን ታሪክ እናገኛለን። የኖህ ዘመን ከሚታወቅባቸው ዐበይት ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የጥፋት ውኃ ነው። ያ ዘመን ሰው ሁሉ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ በአመፅ የተነሣበት፥ ሕገ እግዚአብሔርን የረሳበትና የሥጋውን ፍላጐት ለመፈፀም የተገዛበት ነበር። ይህ የሰው ክፉ ሥራም እግዚአብሔር እንኳ ሰውን በመፍጠሩ እንዲጸጸትና የሰውን ዘር ከምድር ላይ ለማጥፋት እንዲወስን አስገድዶት ነበር።

ይሁን እንጂ ከዚያ ሁሉ ሕዝብ መካከል በአምልኮተ እግዚአብሔር ፀንቶ በሕገ ልቡና እየተመራ በሃይማኖት የተገኘው ኖህ ብቻ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት መልካም ሕይወትን ይዞ በመገኘቱ እርሱና ቤተሰቡ ከሚመጣው አምላካዊ መቅሰፍት እንዲድኑ በፈጣሪው ትዕዛዝ ሦስት ክፍል ያላት መርከብ ሠራ። በዚህ ጊዜ የቀረው ሕዝብ መርከብ በሚሠራው በኖህ ላይ ይሳለቅበት ነበር። ሕዝቡ ከበደሉና ከክፋቱም እንዳልተመለሰ ንስሐም መግባትን እምቢ እንዳለ በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጥፋት ውኃን አዘነበ። ኖህና ቤተሰቦቹ ግን በመርከቢቱ ውስጥ ነበሩና ከጥፋት ውኃው መከራና እልቂት ዳኑ። የቀረው ሕዝብ ሁሉ ምንም የተረፈ ሳይኖር በውኃው ጠፋ።

መርከቢቱ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ኖህ የጌታችን ምሳሌ ነው። መርከቢቱ ባለ ሦስት ክፍል መሆኗ እመቤታችን የሥላሴ ማደሪያ ለመሆኗ ምሳሌ ከመሆኑ በተጨማሪ የድንግል ማርያምን ንጽሐ ሥጋ፥ ንጽሐ ነፍስና ንጽሐ ልቡና ያጠይቃል። የጥፋት ውኃው የምልዓተ ኃጢአት ምሳሌ ነው። ከመርከቢቱ ሳይገቡ ውጭ የቀሩትና በጥፋት ውኃው የሰጠሙት በወላዲተ አምላክ ቃል ኪዳንና በአማላጅነቷ ሳይማጸኑ ቀርተው በትዕቢት ታጅለው በዓለም ሲጨፍሩ በኃጢአት ጌታ በዲያብሎስ የሚጠፉት ነፍሳት ምሳሌ ናቸው። ከኖህ ጋር ወደ መርከቢቱ የገቡት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ሁሉ በወላዲተ አምላክ አማላጅነት በእግዚአብሔር ቸርነት ለመንግሥተ ሰማያት ሕይወት እድምተኞች የሆኑ የምዕመናን ምሳሌ ናቸው። እነዚህ ኃጢአት ሊያጠፉ ቸው ሞት ሊሰለጥንባቸው ከቶውኑ አይችልም (የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ይመልከቱ)።

እንግዲህ ከዚህ ክስተት የምንማረው ምንድን ነው? የሰው ልጅ የእጆቹን ሥራ ለማምለክ ሽቶ ሰማያዊ ፀጋውን በተገፈፈበትና ፈቃደ ሥጋ በሰለጠነበት ክፋትና ኃጢአት አብዝቶ በሚሠራበት አምልኮተ እግዚአብሔር በጠፋበት ዘመን በእግ ዚአብሔር ብቻ ታምኖ መገኘት የሚገባ መሆኑን ነው የምንማረው። የሰው ልጅ ልቡና ለእግዚአብሔር አልገዛም ባለበት በእንደዚህ ያለ ዘመን እንደ ጻድቁ ኖህ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን ያስፈልጋል። ዓለምን የሚያና ውጣትን ሕዝብንና ሕዝብን እያለያየ ሰላምና ፍቅር ነስቶ የሚያበጣብ ጠውን ነፍሳትን በሲኦል ለመለብለብ የሚንቦገቦገውን የእሳት ወላፈን ማለፍ የሚቻለው በእግዚአብሔር ከመታመን ጋር የኃጢአትን ባህር የኢሶልንም የእሳት ውቅያኖስ ቀዝፎ ለመሻገርና ለመዳን የምታስችልና ይህም አምላክካዊ ፀጋ የተሰጣትን አማናዊት መርከብ ገንዘብ ማድረግና በእርሷ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በውስጧ መሰብሰብ አማራጭ የለውም። ይህች መርከብ የባህሩንና የውቅያኖሱን ማዕበል ደረቁንና አስከፊውን አውሎ ንፋስ የሚፋጀውንና የሚንቀለቀለውን ዋእይ ተቋቁማ የምታሻግር ናት። ዛሬ የዓለማችን ሕዝብ ይህችን መርከብ አላወቃትም። በእርሷ ተጠቅሞ የኃጢአትን ባህርና ውቅያኖስ ቀዝፎ ለመሻገር አልቻለም። ስለዚህች መርከብ የሚነገረውን አማናዊ ትምህርት ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ በዓለም የኃጢአት ባህር ውስጥ ተዘፍቆ የሚያ ወጣውና የሚያሻግረው አጥቶ ይታያል። በአማናዊቱ መርከብ በድንግል ማርያም አማላጅነት በመታመን የምንኖር እንደምንድን ተስፋ አለን። ለኖህ ቤዛው የሆነች በኋላም አዳምን ከነበረበት የሲኦል ባህር እንዲወጣ ምክንያት የሆነች እርሷ ቅድስት ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ ከዚህ ዓለም መከራ ነፃ እንወጣ ዘንድ ከሁላችን ጋር እንድትሆን የተዘጋጀ ልቡና ሊኖረን ይገባል። ✣

ይቀጥላል።

# የሽቶው ብልቃጥ

ከዳንኤል ክብረት

ሮማውያን ራሳቸው እየጠሉኝ መጥተዋል። እያንዳንዱ መኰንን የርሱ ብቻ እንድሆንለት ይፈልጋል። ይኸ ደግሞ ለኔ የማይሆን ነገር ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ መኰንን ሊያምነሽንሸኝ የሚችለው ላንድ ሰሞን ብቻ ነውና። የገዛ ወገኖቼ የሆኑት አይሁድማ አክ–እንትፍ ብለው አንቅረው ተፍተውኛል። በመንገድ ሳልፍ አልያም ደግሞ በቤቴ ፊት ለፊት ባለው መንገድ የሚያልፉ ሁሉ ፊታቸውን ኮሶ አስመስለው ምራቃቸውን እየተፉና እየዛቱብኝ፥ አንዳንድ ሴቶችማ እኔን ለማየት ተጸይፈው በዓይነ ርግባቸው ተሸፋፍነው ነው የሚያልፉት።

በተለይ የምኩራብ ሹማምንት ዘንጋቸውን እየነቀነቁ ጥምጣማቸው እስኪፈታ ድረስ በንዴት እየተንዘፈዘፉ ነው የሚያዩኝ። ሊቀ ካህናት ቀያፋና ሐናማ ስለእኔ ኃጢአትና ቆሻሻነት፥ ርኩስነትና ርጉምነት የማያነሱበት አደባባይ የለም። እንደ ህጋቸው እንዳይደበድቡኝ የሮማ መኳንንትን ቀኝ እጂ አድርጌያለሁ። ምን ያርጉኝ ባዩኝ ቁጥር ከመትፋትና ከመፀየፍ በቀር። አንዴ ትዝ ይለኛል፥ በሊቀ ካህናት ሐና መሪነት ምድረ አይሁድ ድንጋይ ተሸክሞ ሊወግረኝ ቤቴ ድረስ መጣ። እኔ ደግሞ ከተባለው መኰንን ጋር ጠጪ እንጠጣ እየተባባልን በመዝናናት ላይ ነበርን። የጫጫታ ድምፅ ስንሰማ ሮጠን ወጣን፥ የኔው ጉድ ኖሯል። የጦር መኰነኑን ሲያዩ ሁሉም ደነገጡ። «እሷ ሮማዊት ናት እኔ በገንዘብ ገዝቼላታለሁ!» ስለዚህ በሮማ ህግ ደግሞ ይሄን የሚከለክል አንቀጽ የለም» ብሎ በተናቸው። ከዚያን ጊዜ ወዲህ አሳቻ መንገድና ጊዜ ጠብቀው «የትውልድ ጠባሳ» ናት ብለው የሚያስቡኝን እኔን ለማጥፋት ጥርሳቸውን ነክሰውብኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሁኔታው እየባሰ መጣ። በኢየሩሳሌም ከተማ በስተምዕራቡ በር ማርታ የተባለች ቆንጆ ሴት የመኰንኖች መቀበያ እልፍኝ በማሠራትዋ ገቢዬ እየቀነሰ አጀብ፥ አጀብ ባዩ እየቀዘቀዘ መጣ። በገዛ ወገኖቼ ላይ ያደረብኝ ሥጋት ግን ዕለት ዕለት እየጨመረ ሄዷል። ከተማ መውጣት አልችልም፥ ከጐረቤቶቼ ጋር አብሬ መብላት፥ መጠያየቅ፥ መረዳዳት ትቼያለሁ። ለቅሶ የሚባል ከደረስኩ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል። ውጪ ናፍቆኛል።

ፍርሃት፥ ጭንቀት፥ ሥጋት ልቤን ይረብሹታል። ከዚህ በላይ ራሴን በራሴ መፀየፍ ጀምሬያለሁ። አብሬ የሆንኩዋቸው ወንዶች፥ ያበጣበጥኳቸው መኰንኖች፥ ለገንዘብ ለወርቅና ለከበረ ዕንቁ ስል እንደ ዕቃ የሸጥኩት አካሌን ሳስበው በውነት አይሁድ እንደሚሉኝ ርኩስ ነኝ ብዬ አስባለሁ። እንዲህ በሰው ሁሉ ተጠልቼ፥ እንደውሻ ተቀጥሮ፥ እንዳረጀ ቁና ተሸቀንጥሮ እስከ መቼ እንደምዘልቀው እንጃ!

ባለፈው ጊዜ ባንድ ሮማዊ መኰንን በኩል ለሊቀ ካህናት ቀያፋ ይቅርታ እንዲያደርግልኝና ወደ ድሮየ እንድመለስ ላክሁበት። ይገርማችኋል «ይቅርታ የሚባል ነገር አላውቅም፥ ዋጋሽ ተወግሮ መሞት ብቻ ነው» የሚል መልስ ላከልኝ። ከዚያ ወዲያ በሬን ቆልፌ ገረዶቼን ሁሉ አሰናብቼ በመኝታ ቤቴ ውስጥ አለቅስ ጀመር።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አንድ ቀን ነው አንዲት የድሮ ጓደኛዬ ከአይሁድ አለቆች ተደብቃ ስጠፋባት ጊዜ ልትጠይቀኝ መጣች። በዕንባ ታጥቤ፥ ሰውነቴ መንምኖ፥ እኔነቴ ጠፍቶ ተጐሳቁዬ አየችኝና በእጅጉ አዘነች። በኋላም ስለከተማው ሁኔታ አንስታ አንዳንድ ነገሮች ታጫውተኝ ጀመር። በዚህ ጊዜ ነው ክርስቶስ ስለተባለው የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ የነገረችኝ ያችን መግደላዊት ማርያምን ከሰው በታች



«አንተ ከመጣሁ ጀምሮ ለራሴ ዘይት አላልከኝም እርሷ ግን በውድ ሽቶ አርከፈከፈችኝ:- በእንባዋም አጥባ በፀጉርዋ ጠረገችኝ።»

አድርጓት ከነበረው ጋኔን እንደፈ ወሳት፥ ከኔ ቤት አቅራቢያ ትኖር የነበረችዋን ደም መፍሰስ ከጀመራት 12 ዓመት የሆናትን ሴት ከበሽታዋ እንደፈወሳት ነገረችኝ፥ «አይጠየፋ ቸውም» አልኳት፥ ኸረ እንዲያውም «ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» ብሏል አለ ችኝ። በልቦናዬ አንድ ነገር አሰብኩ «አሁን የኔንም ኃጢአት ያስተሰርይ ልኝ ይሆን» ብዬ መለስ አድርጌ ደግሞ «አይ እርሱም አይሁዳዊ ነው ዞር በይ ብሎ ቢያባርረኝስ» ብዬ ተጨ ነቀሁ።

«ለመሆኑ እነ ሊቀ ካህናት ቀያፉ ምን ይሉታል??» አልኳት።

«በጭራሽ አይወዱትም፤ እሱ እቴ እውነቷን ነው የሚናገረው፤ ደግሞ የሚውለው ከቀራጩ፥ ከዓሳ አጥማጁ፥ ከኔ ቢጤው፥ ከበሽተኛው ጋር ነው» አለችኝ።

«እሱን የወለደች ማሕፀን ምን የተባረከች ናት» አልኩኝ።

«ቅድስተ ቅዱሳን እንጂ!»

«ልሂድና ችግሬን ልንገረው ብለሽ?»

«ሂጅ ከጠበቅሽው በላይ ሆኖ ታገኝዋለሺ።»

በነጋታው ቤቴን ሸጥኩት። 500 ዲናር አወጣ። «ምን ይዤ ልሂድ» ብየ ማሰብ ጀመርኩ። ልብስ፥ ግን ምን ያደርግለታል። ምግብም ራሱ አበርክቶ ማብላት የሚችል ነው አሉ። ብዙ ነገሮችን አወጣሁ አወረድኩ። ገንዘቡንም እንዳልሰጠው ‹የቄሳርን ለቄሳር› ብሏል ብለውኛል። ታዲያ ምን ላድርግ። አዎ ወንዱን ሁሉ ሳታ ልልበት፥ ራሴን እንደ ሴት አማልከት ስቆጥርበት የነበረውን ሽቶ ገዝቼ እግሩ ሥር መስበር አለብኝ ብዬ ወሰ ንኩና ከርሱ ይቅር ባይነት የማገኘው ደስታ ቡተስፋ እያፍነከነከኝ በሩጫ ረስቼው በከረምኩት የኢየሩሳሌም አደባባይ ተፈተለክሁ። አንዳንዱ ዕብድ መስየው አፍጦ ያየኛል፥ ሌላው እኔ መሆኔን ሲያውቅ ድንጋይ ፍለጋ መሬት መሬት ያያል። የቀረው ደግሞ እንዳልነካውና እንዳላረክሰው መንገድ ለቅቆ ይሸሻል። እኔ ግን ለሁሉም ግድ አልነበረኝም። ብቻ ወደ ሽቶ መደበር!

«ሽቶ...ሽቶ...ሽቶ ሰጠኝ» አል ኩት ከሱቋ ውስጥ ያሉት ጐረምሶች እኔነቴን ሳይለዩ አልቀሩም ይጠቋ ቆሙብኛል።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

«የስንት ዲናር?» አለኝ።

«የ300» አልኩት።

«አ.አ! እኔም ራሴ ይኸንን ያህል ገንዘብ አይቼ አላቅም» አለኝ ትቼው ወደሌላ መደብር ሮጥኩ።

«እባክህ ሽቶ ስጠኝ ወንድም።»

«የስንት?»

«የ300 ዲናር።»

«እኔን ጨምረሽ ትገዥኝ እንደሆነ እንጂ ይህንን ያህል የሚያወጣ የለኝም» ነገር ግን እዚያ ማዶ የነሰሎሞን ሽቶ አለ ይባላል ጠይቂ።»

ልቤ እየተፍነከነከ ወደ ጠቆመኝ መደብር ተፈተለኩ። «ሽቶ...ሽቶ... ሽቶ...ስጠኝ።»

በችኮላየ ተደናግጦ አፍጥጦ አየኝ። ዝቅ ሲል ጊዜ ሊወግረኝ ነው ብዬ ደነገጥኩ።

«ምን ያህል የሚያወጣ።»

«የ300 ዲናር» አላመነኝም መሰል ይበልጡን አፈጠጠብኝ። ነፍስና ሥጋየ ሊለያዩ ደረሱ።

«አንድ የነሰሎሞን ዘመን ሺቶ ነበር» አለና ወደውስጥ ገብቶ አወጣና ሰጠኝ። ዲናሩን ወርውሬለት ሽቶውን የመቀማት ያህል ነጥቀው በኢየሩሳሌም ዋና ጐዳና በዓይነ ርግቤ ራሴን ሰውሬ ሮጥኩ፣ ልቤ በፍጥነቱ ሊተረተር እስኪደርስ በረርኩ ከመቼው ደርሼ የተጫነኝን የኃጢአት ሸክም እንደማወርድ በጣም ቸኩያለሁ። በጐዳናው ታልፍ የነበረች አንዲት ወይዘሮ ጠጋ ብያት «ክርስቶስ የት ነው» አልኳት። በፈሪሳዊው በስምዖን ቤት ነው» ብላ ጥላኝ ሄደች።

ተስፋዬ የመነመነ መሰለኝ። እንኳን ፈሪሳዊው ተራው ዜጋ ጠልቶኛል። ስምኦን ካየኝ ደግሞ ወዲያው ነው ጥሬ ሥጋዬን የሚበላው። ለተወሰኑ ጊዜያት በጐዳናው ዳር ቆሜ አመንታሁ። በመጨረሻም የመጣው ይምጣ ብዬ ወደ ፈሪሳዊው ስምዖን ቤት በረርኩ።

ግቢው ክርስቶስን ተከትለው በመጡ ሰዎች ተጨናንቋል። መግቢያ መውጫው አይታይም። ሁለት ወታደሮች ግቢውን ግራ ቀኝ ሆነው ይጠብቁታል። ጠጋ ብዬ «ክርስቶስን ፈልጌ ነበር» አልኩት በግራ የቆመውን ዘበኛ።

«ዞር በይ ሥራ ላይ ነው» አለኝ። ዕንባ ተናነቀኝና:—

«ኧረ እባክህ ለአንዲት ደቂቃ ብቻ ነው» አልኩት።

«ማነሽ ለመሆኑ» ትኩር ብሎ አየኝና

«ማርያም ዘማዊቷ አንቺው ነሽ...ዞር በይ ጥፊ ከፊቴ»

አለና በትሩን አነሳብኝ። ዕድሌን እያማረርኩ ምርር ብዬ አለቀስኩ፣ ተንሰቀሰቅኩ።

ከውስጥ የአንድ ቅላጼው የሚያምር ሰው ድምፅ ተሰማ። ሁሉም ነገር ፀጥ አለ። «ጴጥሮስ፣ ከውጭ የምሰማው ድምፅ ምንድነው። እስቲ ወጣ በልና ተመልከት» አለው። አንድ ሺበታም ሰውየ ወጣ አለና ዘበኛውን አነጋግሮት ገባ።

«አንዲት ዘማዊት ናት ለክርስቶስ ካልሰገድኩ ነው የምትለው።»

«አስገባት።»

ጉርምርምታ ተሰማኝ። የስምዖን ፈሪሳዊ ድምፅም «የማናት ቀባጢ አታባርሩዋትም» ይላል።

ጴጥሮስ የተባለው ወጣና «አስገቡዋት ተብሏል» ብሎ ለዘበኛው ነገረው ደንግጦ አፈጠጠባት።

«እንዲ ምን መሆናችሁ ነው። ዘማዊት እኮ ናት፣ መወገር አለባት ቤቱን ታረክሳለች፣...አትገባም» አለው።

«ጌታ ነው ያዘዘው» ብሎት ገባ።

«ግቢ!» አለኝ እንደ ብራቅ ጮኾ።

እየተንቀጠቀጥኩ ስገባ የተሰበሰቡት ሁሉ እንዳልነካና እንዳላረክሳቸው መንገድ ለቀቁልኝ በዕልፍኙ በር ስገባ ምድረ ፈሪሳዊ ተሰብስቧል። እያጉረመረሙ ተነሱና ሸሹኝ። ፈጠን ብዬ እግሩ ሥር ተደፋሁ የሺቶውን ጠርሙስ ሰብሬ ገላውን አርከፈከፍኩት፣ በዕንባዬ እግሩን እያጠብኩ በፀጉሬ አሸሁት። ልዩ የሆነ የደስታ ስሜት ውስጤን ያበራዋል። እንደ ሸክም የከበደኝ ነገር ሲነሳ ይታወቀኛል። የፈሪሳውያን ማጉረምረም አላበቃም። እኔም በደስታ እያነባሁ እግሩን በፀጉሬ ጠረግኩት።

ስምዖንም «ምነው አምላክ ነኝ እያለ እንዴት ይቺ ዘማዊት ስትዳስ ሰው አውቆ አያባርራትም» አለ።

«ስምዖን ሆይ» አለው ክርስቶስ


«አንተ ከመጣሁ ጀምሮ ለራሲ ዘይት አላልከኝም። እርስዋ ግን በውድ ሺቶ አርከፈከፈችኝ። አንተ ለእግሬ ውሃ አላልከኝም። እርሷ ግን በዕንባዋ አጥባ በፀጉርዋ ጠረገችኝ ብዙ ሺታለች፣ ብዙ ወዳለችና የበዛው ኃጢአቷ ተሠርዮላታል» አላቸው። ሐዋርያቱ ራሳቸው ደንግጠዋል። እኔን የመሰለ ታዋቂ ዘማዊ፣ ርኩስ ተብዬ እንደ ውሻ የተናቅሁ ሰው በአንድ ጊዜ ኃጢአቴ ሲሰረይ። ይህንን ያየው የባህርይ አምላክም ወደ ሐዋርያት ዞወር ብሎ «ወንጌል በተሰበከበት ቦታ ሁሉ የርስዋ ታሪክ ለመታሰቢያ ይነገራል» ብሎ አዘዛቸው። ወደ እኔም ዞወር ብሎ «ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል» አለኝ። ታላቁ ሸክም ቀለለኝ፣ ርኩስነቴ ቀረ፣ አዲስ ሰው ሆንኩኝ ያውም ከታላቅ ክብር ጋር። ✣



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

በዚህ ዓምድ ገዳማትን፥ አድባራትን፥ ታሪካዊ ቦታዎችን፥ የቤተክርስቲያን አባቶችንና ሌሎችንም እናስተዋውቃለን። የመጽሔታችን አንባቢያንም በዚህ ዓምድ ሥር ሊቀርቡ የሚችሉትን ከበቂ ማስረጃ ጋር ቢልኩልን በደስታ የምናስተናግድ መሆኑን እየገለጥን ለዛሬው ግን የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤልን ገዳም ይዘንላችሁ ቀርበናል።



የሐመረ–ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የመግቢያ በር


ከአዲስ አበባ አንድ መቶ ስድሳ ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የደቡብ ሸዋን ዋና ከተማ ዝዋይን ያገኛሉ። የዝዋይ ከተማ ግማሽ ገጽታ የሚዋሰነው በስምጥ ሸለቆ ውስጥ በስፋቱ በሚታወቀው የዝዋይ ሐይቅ ነው። ሐይቁ ከከተማው በስተምሥራቅ ተንጣሎ ይገኛል። የደቡቡን የሐይቁን ክፍል ተከትሎ የሚሄድ ሰው ከአምስት ኪ.ሜትር ርቀት ላይ አንድ ዙሪያው በቆንጥርና በቃጫ ተክል የተከበበ ግቢ ያገኛል። በግቢው መግቢያ ላይ በብረት ቅስት የተጻፈ «ወደ ሐመረ–ብርሃን ቅዱስ ገብር ኤል ገዳምና የካህናት ማሰልጠኛ» የሚል ጽሑፍ አለ።

ገና የገዳሙን በር እንደገቡ በቀኝ በኩል የፓፓየ ተክልና በግራ በኩል ደግሞ የእህል ወፍጮ ቤትና የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ትንሽ ክፍል ቤት ይታያል። ከመግቢያው ጀምሮ ጠጠር የተነጠፈበትንና በግራና ቀኙ አርዘሊባኖስ የተተከለበትን መንገድ ተከትለው ወደምሥራቅ ሲዘልቁ የሚያገኙት የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤልን ቤተክርስቲያን ነው። ቤተክርስቲያኑን ተሳልመው ይትዎን ወደ ደቡብ ሲያዞሩ የክርስትና ቤቱን (ፈለገ ዮርዳኖስ) ያገኛሉ። እንደገና ፊትዎን ወደ ምዕራብ ሲያዞሩ አንድ ዘመናዊ ሕንፃ ያገኛሉ። ይህ ሕንፃ ድርሐ–ጽዮን በመባል የሚታወቅ አንድ የምግብ አዳራሽና አሥር ክፍሎች ያለው የእንግዳ መቀበያ አለው። ክፍሎቹ በላሊበላ አብያተ መቅደስ ተሰይመዋል። ውስጡ በዘመናዊ ፕላን የተሠራ በመሆኑ እያንዳንዱ ክፍል በውስጡ ሁለት አልጋዎች፥ መጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ያለው ነው። በዚህ የእንግዳ መቀበያ በረንዳ ላይ ተቀምጠው ከሰሜን በኩል ከተንጣለለው የዝዋይ ሐይቅ የሚነፍሰውን ቀዝቃዛ አየር እየተጎነጩ የሚያዳምጡት የአእዋፍን ዝማሬ ነው። በዚህ ጥቂት ከአረፉ በኋላ የገዳሙን የውስጥ ይዞት ለመመልከት ጉብኝት ሲጀምሩ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተደቡብ ካሉት የመማሪያና የተማሪዎች መኖሪያ ሕንፃ እንዲሁም ከምግብ አዳራሹና ከማብሰያው ሕንፃ በስተጀርባ በአረንጓዴ ተክል ያጌጠና ዓይንን የሚማርክ ግቢ ያገኛሉ። በውስጡ በመስመርና በጥንቃቄ ዘመናዊ የእርሻ ጥበብን ተከትለው የተተከሉ ከ700 በላይ የሚሆኑ የብርቱካን ተክሎች ይገኛሉ። ሁሉም በላያቸው በተንዠረገገው ፍሬአቸው ክብደት ለመቆም የተቸገሩ ይመስላሉ። በእነዚህ ተክሎች መካከል የቲማቲምና የቃሪያ ተክል ይገኛል። እያንዳንዱ የብርቱካን ተክል በሥሩ ዙሪያ አፈር ታቅፎ ውኃ ከሚያገኝበት የመስኖ ቦይ ጋራ ተገናኝቷል። የውኃውን ቦይ ተከትለው ሲሄዱ ወደ ሐይቁ ሌላኛ ጠርዝ ይደርሳሉ። በዚያ አራት የሚሆኑ ትላልቅ በናፍታ የሚሰሩ የውኃ ሞተሮች አሉ። እነዚህ ናቸው የብርቱካኑንና የፓፓዬውን አትክልት ውኃ የሚያጠጡት።

·ከብርቱካኑ ተክል አንፃር የደን ያህል እጅግ ብዙ የሆነና ቁጥሩ ወደ 12000 የሚደርስ የሙዝ ተክል አለ። እንደ ብርቱካኑ ሁሉ በመስኖ ሥርዓት ውኃ የሚያገኝ ሲሆን የሚያፈራው ፍሬ ሳይወድ በግዱ ትሁት እንዲሆን አድርጎት አጎንብሶ ነው የሚታየው። በሙዙ ተክል መካከል አልፈው ወደምሥራቅ ሲሄዱ በስተደቡብ ያለውን የሐይቁን ክፍል ያገኛሉ። ከዚህ ጀምሮ የገዳሙን ዙሪያ የሚከበውን ከ200000 በላይ የሆነ የባህር ዛፍ ተክል ይመለከታሉ:- ገዳሙ በአሁኑ ጊዜ ለሚሠራቸው ሥራዎችም ሆነ ለማገዶ የእንጨት ችግር የለበትም። በባህር ዛፍ በተከበበው በዚህ ገዳም ውስጥ ቁጥራቸው ከአሥራ አምስት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org



በገዳሙ ውስጥ ካሉት ትውፊታዊ የቤተክርስቲያናችን መማሪያዎች መካከል አንዱ የሆነው የዜማ መማሪያ

በላይ የሆኑ የቀንድ ከብቶችና አንድ አህያ የሚሠማሩበት ጋጣና የሚያድሩበት በረት አለ። ከዚህ አልፍ ብለው ደግሞ የቀድሞውን የአብነት ትምህርት የሚያስታውሱ ጥንታውያን የመማሪያ ሥፍራዎች አሉ:- እነዚህ የቅዳሴ፥ የዜማ፥ የንባብና የመሳሰሉት ትምህርቶች የሚሰጡባቸው ትውፊታዊ መማሪያዎች ናቸው። ከዚህ ሌላም በውስጡ 8000 ትሪማንቱሪ፥ 400 አርዘሊባኖስ፥ 436 የቡና ተክልና 300 የፓፓያ አትክልት አሉበት።

ከእነዚህ በተጨማሪ ገዳሙ እንደሌሎች ገዳማት ሁሉ የንግህና የሠረከ የማኅበር ጸሎት እንዲሁም የአንድነት የማዕድ ሥርዓት የሚከናወንበት ሲሆን በየጊዜው ከሚገቡት የማሠልጠኛው ተማሪዎች ሌላ ከሁለት መቶ የማያንሱ አዳሪ ተማሪዎች አባቶች መነኮሳትና መምህራን ያሉት ሲሆን የሚመራውም በአበምኔት ነው። እንግዲህ የዝዋይ ሐመረ–ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በውስጡ የካህናት ማሠልጠኛ ያለው ጭምር በመሆኑ በሚቀጥለው እትማችን የገዳሙን የአመሠራረት ታሪክና የማሰልጠኛውን ይዞታና የሥራ ፍሬ በያዘው ዝግጅት እስከንገናኝ ቸሩ እግዚአብሔር በረድኤት ጠብቆ ያገናኘን። ✥

ይቀጥላል።

## ጥቅሶች

«ሰውነታችሁን ለዐመፃ፥ ለኃጢአት መሣሪያ አታድርጉት፥ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሳ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጉ እንጂ፤ ሰውነታችሁንም ለእግዚአብሔር የጽድቅ መሣሪያ አድርጉ።»

ሮሜ 6፥13

«ነፍስ ሥጋን ካላሸነፈቻት እንግዲህ ሥጋ ለነፍስ መቃብር ሆነች ማለት ነው።»

ፈላስፋው ፒታጎሮስ

ዓለም ስትመጣ ለሰው የሌለውን ገንዘብ አምጥታ ትሰጠዋለች። ስታልፍበት ደግሞ የራሱን ወስዳ ለሌላው ትሰጥበታለች።»

ከፈላስፎች አንዱ

«ስለዚህ የጭንቅ ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ»

መክብብ 12፥1

«ኃጢአትን አትሥራት መከራ አያገኝህም። ከበደል ራቅ። እሷም ካንተ ትርቃለች። ፍዳን ሰባት እጥፍ አድርገህ እንዳትቀበላት በሰውነትህ ኃጢአት አትሥራ።»

ሲራክ 7፥1–3

«በመባዬ (በማቀርበው መሥዋዕት) ብዛት እግዚአብሔር ኃጢአቴን ያስተሠርይልኛል መባም ካገባሁ ገናና እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል አትበል»

ሲራክ 7፥9

«በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጁ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና፤ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጁ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው»

ማቴ 7፥13–14

«እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ»

ማቴ 7፥1–5

የምግባር ጉድለት የቆዳ በሽታ ነው። የሃይማኖት ጉድለት ግን የልብና የኩላሊት፥ የሳንባና የጉበት፥ የሆድና የአንጀት ደዌ ስለሆነ ይብሳል። ለውስጥ ሰውነት መከላከያው ቆዳ እንደሆነ ሁሉ ለሃይማኖትም ምሽጉ ምግባር ነው። ምግባር ከተጣሰ ሃይማኖት መናወጡ አይቀርምና።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

በዚች ዓምድ ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ኑሮአችን ልንመስል የሚገባንን በኅብረተሰብ መካከል አገላለጣችን ምን መሆን እንዳለበትና የኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ኑሮ በምን ላይ ተመስርቶ የሚመራ ሊሆን እንደሚገባው ለማውሳት ይሞከራል። ለዛሬው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱን የክርስቲያን ቤተሰብ ሕይወት ለመዳሰስ አስበናል።

## የሮማው መቶ አለቃና ቤተሰቡ

የሐዋርያት ሥራን እያነበብን እስከ ዘጠነኛው ምዕራፍ ከተጓዝን በኋላ አሥረኛውን ስንጀምር አንድ አስደናቂ ታሪክ እናገኛለን። ታሪኩ በምዕራፉ በሙሉ የተፃፈና ስለ አንድ ሮማዊ የመቶ አለቃ የሚተርክ ነው። ከሮማ መኮንኖች መካከል የሆነው ይህ ሰው ቆርኔሊዎስ ይባላል። ነዋሪነቱ በዚያ ዘመን በእስራኤል የሮማ መንግሥት የሀገር አስተዳደር ዋና መንበር በሆነችውና እስከ መቶ ሺህ ለሚደርሱ ሰዎች መናኸሪያ በሆነችው ቂሣርያ ነበር።

የመቶ አለቃ ቆረኔሊዎስ ከአህዛብ (ካልተገረዙት) ወገን የተገኘ ከቤተሰቡ ጋር እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያመልክ፥ የሚመፀውት፥ ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት በመነጋገር የሚኖር ሰው ነበረ። አንድ ቀን በዘጠኝ ሰዓት ከቤተሰቡ ጋር በጸሎት እየተጋ ሳለ ያላሰበውና ያልተጠበቀ ነገር አጋጠመው። ይኸውም ጸሎቱና ምፅዋቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚያበስር ዜና ብሥራት ነበር። ድምፁን ያሰማው መልአክ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ ግርማ ተገልጦ አነጋገረው። ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ አርጓል አለው። በዚህ የምሥራች ቆርኔሊዎስ ተደናግጦ ሳለ መልአኩ ለሚኀድልህ ነገር ሁሉ ፈጥነህ ሰዎችን ወደ ኢዮጴልከህ ጴጥሮስን አስጠራ እርሱም ልታደርግ የሚገባህን ይነግርሃል ብሎት የቅዱስ ጴጥሮስንም አድራሻ ሰጥቶት ተሰናበተው።

ቆርኔሊዎስም ሳይዘገይ ከአገልጋዮቹ ታማኞቹን ጠርቶ የሆነውን ሁሉ ከተረከላቸው በኋላ ወደ ኢዮጴ ላካቸው። ከሦስት ቀናት በኋላም ቅዱስ ጴጥሮስን ይዘው ተመለሱ። በቂሣራያም የመቶ አለቃው ቤት በብዙ ሰዎች ተሞልታ ተጨናንቃ ነበር ቆርኔሊዎስ የበረከቱ ተካፋዮች የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ታዳሚዎች ይሆኑ ዘንድ ዘመዶቹን፥ የቅርብ ወዳጆቹን፥ እንዲሁም የአካባቢውን ሕዝብ ሁሉ ጠርቶ ነበርና።

ለተሰበሰበው ሕዝብም ከአራት ቀናት በፊት ያጋጠመውን ነገር ሁሉ ዘርዝሮ ተናገረ ቀጥሎም ቅዱስ ጴጥሮስን «እንግዲህ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዝከውን ሁሉ እንድንሰማ እኛ ሁላችን አሁን በእግዚአብሔር ፊት በዚህ አለን» ብሎት ልቡን ከፍቶ ለእግዚአብሔር አቀረበ። ይህ ሃሳብ የቆርኔሊዎስ ብቻ ሳይሆን የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ሃሳብ መሆኑን አምኖ ነው የተናገረው። ይህ ንግግር እራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ልቡናውን በእግዚአብሔር ፊት የጣለ ራሱን ያዋረደ ሰው ንግግር ነበርና ቅዱስ ጴጥሮስም ተገቢውን የእግዚአብሔር ቃል ለተሰበሰቡት ሁሉ ሰበከ። ሁሉም ሰዎች በእውነትና በመጸጸት በእግዚአብሔር ፊት ልቡናቸውን ከፍተው የሚነገረውን የእግዚአብሔር ቃል ይሰሙ ስለነበር መንፈስ ቅዱስ ኀበኛቸው በልቡናቸውም አደረ የእነዚህን የአሕዛብ ሰዎች ልቡናም ለወጠ ለእምነትም አዘጋጃቸው ተጠመቁም ክርስቲያኖችም ሆኑ መልካሙ ዝናቸውም እስከ ይሁዳ ድረስ ተሰማ የሕይወት ብርሃንም በዚያ በራ።

ክርስቲያኖች እስቲ የዚህን ቤተሰብ ሕይወትና ፍሬ በአንክሮ እንመልከትና ኦርቶዶክሳውያን ቤተሰቦች ምን መምሰል እንደሚገባን እናስብ፤ የቆርኔሊዎስ ቤት የእውነተኞች ሰዎች የትክክለኞች ክርስቲያኖች የጠንካራ ምዕመናን ቤት ነበር። ቆርኔሊዎስ ቤቱን ይመራ የነበረው በጸሎት ነበር። ቤቱ የጸሎት፥ የምስጋና፥ የትሩፋት፥ ሕይወቱም የሰላም፥ የፍቅር፥ የደግነት፥ ብቻ፤ በእግዚአብሔር ፊት የነበረው መመላለስ ያማረ ስለነበረ የእግዚአብሔር መልአክ ወደዚያ ቤተሰብ መጣ የኑሮ መመሪያንም ሰጠው ምን ሊያደርግ እንደሚገባው ነገረው። ዛሬ በዓለማችን ላይ እጅግ ብዙ ቤተሰቦች አሉ የኑሮአቸው መሠረት ግን እንደ ቆርኔሊዎስ ቤተሰብ ያለ በእግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሕይወት አይደለም። በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ ያልተመሠረተ ሕይወት ያለው ቤተሰብ ጎደሎ ነው። ክርስቶሳዊ ያልሆነ፥ ፍቅርን የማያውቅ፥ ሰላም የሌለው፥ ከሕብረት የራቀ የማይተማመን በመሆኑ ሕፁፅ (ጎደሎ) ነው። በብዙ ሥፍራዎች የምናያቸው ቤተሰቦች ይህን ይመስላሉ።

ቤተሰቦች ግን የመቶ አለቃውን የመሰሉ ሊሆኑ ያስፈልጋል አንድ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ልብ አንድ ቃል አንድ ሐሳብ፥ አንድ ሕይወት ያላቸው መሪያቸው እግዚአብሔር፥ መሣሪያቸው ጸሎት ሥራቸው ትሩፋት ፍሬአቸው ከንጹሕ እምነትና ከቀና ሥነ ምግባር የተገኘ ሕይወት መሆን አለበት። ይህን የመሰለው የቤተሰብ ሕይወት የእግዚአብሔርን ትኩረት የሚስብ ከመሆን ጋር በእግዚአብሔር ለመባረክ ዕድል ያጋጥመዋል። ለዚህ ነው የቆርኔሌዎስ ቤተሰብ በእግዚአብሔር ፊት ያማረና በመንፈሳዊ ትጋት በክርስቲያናዊ ትሩፋት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በእግዚአብሔር መልአክ ለመጎብኘት በመልአኩ አንደበት የተነገረ የምሥራች ለመስማት የታደ የሆነው። የክርስቲያን ቤተሰቦች በተለይም የኦርቶዶክሳውያን ኑሮ እንዲህ ሊሆን ያስፈልጋል። በጾምና በጸሎት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ያለው ቤተሰብ ድንገት ሳያስበው እንደቆርኔሊዎስ የምሥራች ሊሰማ ይችላል ሕይወቱ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋራ የተያያዘ የሚያደርገውን እግዚአብሔር የሚነግረው በቅዱሳን የሚጎበኝ ቅዱሳንንም እንደ ቆርኔሊዎስ ሁሉ ለመቀበል የተዘጋጀ በክርስትና ኑሮዬ ምን ላድርግ ብሎ የሚጠይቅ ከልቡ የሚያምንና ከልቡ የሚጸልይ ለትሩፋት ሥራ አበክሮ የሚተጋ ቤተሰብ ነው ኑሮውና መንፈሳዊው ሕይወቱ በእግዚአብሔር የሚጎበኝለት።

እንግዲህ ክርስቲያኖች እስቲ የየራሳችንን ቤተሰብ ለአንድ አፍታ መለስ ብለን እንመልከት፤ ክርስቲያኖች ነን ብለን በክርስትናችን ከመመላለስ አልፈን በየቤታችን ያለው ኑሮአችን የቱን ያህል የተለወጠና ከእግዚአብሔር ጋርስ ያለን ግንኙነት በጾምና ጸሎትስ ያለን ትጋት ምን ያህል ነው? በኑሮአችን ስለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርና መላእክቱ እንዲሁም ቅዱሳኑ የሚጎበኙት መንፈስ ቅዱስም ሊያድርበትና ሥራ ሊሰራበት የተዘጋጀ ልቡና አለን ይሆን? ወይስ በአንፃሩ ቤታችን የጠብና የክርክር፥ የንትርክና የጥላቻ፥ የአሉባልታና የሐሜት፥ የማመንዘርና የስካር ቤት ይሆን። ቤተሰባችንስ በተገናኘ ጊዜ ሁሉ ሃሳቡ አድማናጥል ቂምና በቀል ይሆን ወይስ እንደቆርኔሊዎስ ቤተሰብ የሚያመስግንና ነገረ እግዚአብሔርን የሚያመላልስ በውኑ በየቤታችን ፍቅር፥ ትህትና፥ መከባበር፥ መተባበር፥ መተዛዘን፥ መተሳሰብና በአጠቃላይ የክርስትና ሕግጋትና የቤተክርስቲያኒቱ ሥርዓት አለን? ለወልደ አምላክ ቃል ለወንጌል የሚታዘዝ ልቡና የተለወጠ ሕይወት የቤተሰባችን መታወቂያ ሊሆን ያስፈልጋል።

የክርስቲያኖች ቤተሰብ የልጆች ተስፋ የወደፊት የሕይወታቸው መርሕ ደስታቸውና ሰላማቸው ነውና የቤተሰቡ መሪዎች አባትና እናት የሚኖራቸው ፍጹም መንፈሳዊ ሥነ ምግባርና ክርስቲያናዊ ሕይወት የልጆቻቸውን አእምሮ በመቅረጽ የሚኖረው ሚና እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ያስፈልጋል የልጆች የመጀመሪያ ት/ቤታቸው ቤተሰብ ነው። ስለዚህ ከቤተሰቡ ኃላፊ ሃይማኖትን፥ ምግባርን፥ ሥርዓትንና ትውፊትን ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ማኅበራዊ የክርስቲያኖች ሕይወትን ጭምር እንጂ ፀብንና ክርክርን፥ ጥላቻንና ሰላምን የሚነሳ ንትርክን፥ ስካርንና አሉባልታን መማር የለባቸውም።

ከእነዚህ ይልቅ መዘመርን፥ መጸለይን፥ ቅዱስ መጽሐፍንና ሌሎችን አዋልድ መጻሕፍትን ማንበብ ከሚያውቅ ቤተሰብ የሚገኙ ልጆች ደግሞ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ማመስገንን የለመዱ ፍቅርንና መተሳሰብን ገንዘብ ያደረጉ የእምነትና የሕይወት ሰዎች ሀገራቸውን የሚወዱ በሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር የታነፁ በህሊናቸው ክርስትናና ክርስቲያናዊ ሕይወት የሠረፀ ይሆናሉ። ይህን የመሰለው ሕይወት ከቤተ ክርስቲያናችን ምዕመናን የሚገኝ ፍሬ ሊሆን ይገባል።

ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ እንደ ኤልሳቤጥና ዘካርያስ በችግርና በፈተና ጊዜም የሚፀና (ሉቃ 1፥1–25) መካንነት ድህነትና በሽታ የማይለየው የሃሜት ጦር ወግቶ የማያቆስለው በቃለ እግዚአብሔር የታነፀ በክርስቲያናዊ ፍቅር የፀና ግንብ ነው። ከዚህም በተጨማሪ እንደቀደሙት አበው እንደ አብርሃምና ሣራ ቤት ያለ በፍቅርና በሰላም የታነፀ እንግዶች የሚስተናገዱበት የማርቆስን እናት የማርያምን ቤት የመሰለ መሆን ይኖርበታል። በእንዲህ ያለ ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ አባትና እናት ለጸሎት የሚተጉ ለልጆቻቸው የሃይማኖታቸውን ትምህርት የሚያስተምሩ (2ጢሞ 1፥5–1) ዘወትር ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ )1ኛ ሳሙ 1፥1–11) ከሆነ ልጆቻቸው ደግሞ እንደመጥምቁ ዮሐንስ ከስካር፥ ከዝሙት፥ ከክፋትና ከተንኮል፥ ከዓለማዊ ፈቃድ የተለዩ (ሉቃ 1፥13–15) እንደ ይስሐቅ ቅንና ታዛዥ (ዘፍ.27፥1–12) ይሆናሉ በዚሁም በእግዚአብሔር ፊት መወደድንና ሞገስን ያገኛሉ።

ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ የሚመራው በንስሐ ሕይወት ነው (ሉቃ 5፥14) የቤተሰቡም አባላት ከኃጢአት የራቁ ጽድቅን የሚናፍቁ ሥጋዊ ፈቃዳትን የሚንቁ በንስሐ እየታጠቡና ለዘለዓለማዊ ሕይወት የተዘጋጁ ራሳቸውንም ለቅዱስ ሥጋውና ለክቡር ደሙ ማደሪያ አድርገው የሚያቀርቡ ከሆነ የቤተሰቡ የኑሮ መሠረት ፍቅርና ሰላም ነው!! (1ኛ ቆሮ. 13፥1–13) የዚህም ቤተሰብ ልጆች የሚታወቁት በሃይማኖት የታነፁ በምግባረ ክርስትና የፀኑና በውስጣቸው ቅንነት ቸርነትና በጎነት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የተዋሐዳቸው የመመላለስ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ሰዎች በመሆናቸው ነው። በአጠቃላይ ኦርቶዶክሳዊ የሆነ የክርስቲያን ቤተሰብ መሠረቱ ትዕዛዛተ ኦሪትና ሕግጋተ ወንጌል በመሆናቸው በአለት ላይ የተመሠረተ ከመሆኑ የተነሣ የፀናና የማይናወጥ ነው (2ጢሞ. 1፥5) 1ኛ ቆሮ.1፥1–7 (ቲቶ 2፥5–10)

እንግዲህ በዚህ ሕይወት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችንን አውቀን ለሥርዓቷና ለትውፊቷ የሚገዛ ለአበው ሊቃውንት ትምህርት የሚታዘዝ ሕይወት ያለው አማናዊ የሆነ እግዚአብሔር የቀረበው እንደ ቆርኔሊዎስ ቤተሰብ ያለ መላዕክት የሚጎበኙት ቅዱሳን በፀጋ የሚያገለግሉት እግዚአብሔር የሚደሰትበት መንፈስ ቅዱስ የሚቃኘው ቤተሰብ እንዲኖረን የአምላክ ፈቃድ የወላዲተ አምላክ ረድኤት አይለየን። ✣

«ልጂ የዓለም ፍቅርና ጣዕሟ እንዳያስትህ ተጠንቀቅ። እርሷ ከአንተ በፊት ለነበሩት አልነበረችላቸውም፤ ዛሬም ለአንተ አትኖርልህም፤ እንደአንተ ላሉትም አትኖርባቸውምና።

ሶቅራጥስ

እንዲሁም «ዓለም አስቀድማ ከምትንቅህ አንተ አስቀድመህ ናቃት። ባትንቃትም እርሷ ወረተኛ ናትና ሳትንቅህ አትቀርም።»

ከሊቃውንት

ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን ክፉውን ነገር ተጸየፉት ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ ለጌታ ተገዙ በተስፋ ደስ ይበላችሁ በመከራ ታገሡ በጸሎት ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።» ሮሜ 12፥8–13

# በረከተ ወንጌል

ከዲ.እሸቱ ታደሰ

በዚች ዓምድ ሥር የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሚያስተምረንን ሕይወት እንማራለን። ስለዚህም ከቅዱስ ወንጌል በረከት የምንሳተፍበት በመሆኑ ዛሬ ወንጌል ማለት ምን ማለት ነው? ከሚለው ጥያቄ መነሳቱ የሚበጅ መሆኑን እናምናለን።

ወንጌል የሚለው ቃል ዮአግሊዮን ከሚል የግሪክ ቃል የወጣ ሲሆን ፍችው የምሥራች ማለት ነው። የምሥራች የተባለበት ምክንያት አዳምና ዘሩ ከፍዳና ከመከራ የሚድኑበት ዘለዓለማዊ ድኅነት የተገኘበት፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መታረቁ፥ በሰዎች ላይ የሠለጠነው ሞት በእግዚአብሔር ሞት ድል መነሣቱ የተረጋገጠበት፥ አዲሱ ኪዳን እርሱም በክርስቶስ መሥዋዕትነት ሰላም መሆኑ የተነገረበት ስለሆነ ነው።

ከዚህ የሰላም፥ የድኅነት፥ የደስታ፥ የዘለዓለማዊ ተስፋና ሕይወት የምሥራች መስማትና ከበረከቱ መሳተፍ የሚያስፈልግ ቢሆንም ዓለምና የዓለም ወገኖች ሁሉ ለዚህ ማዕድ የተዘጋጀ ሕይወት በማጣታቸው የሞተላቸውን አምላክ ትተው የገደላቸውን ጠላት ዲያብሎስን በማምለክ በተሠወረ ግዞት ተይዘው ይገኛሉ። ታዲያ በጌታችን በመድኃኒታችንና በአምላካችን ቅዱስ ወንጌል ለዓለም ሕይወት መንገርና ዓለማውያን የሆኑትን ለሕይወት መጥራት አስፈላጊ በመሆኑ ሐመር ኦርቶዶክሳዊት መጽሔታችን በበረከተ ወንጌል ለሕይወት ልትጠራን በከፍታው ቦታ ላይ ቆማ በልቡናው አላዋቂ ቢኖር ወደዚህ ጠጋ ይበል ከወንጌል በረከትም ይሳተፍ ትለናለች።

በዚሁም መሠረት ከቅዱስ ወንጌል አንዱን (የሉቃስን ወንጌል) መሠረት በማድረግ በተከታታይ ሐመር ያዘጋጀችውን የበረከተ ወንጌል ፍሪዳና የጠመቀችውን ወይን ሕይወት ታቀርባለች። እንግዲህ ከዚህ ድግስ ለመሳተፍና ከበረከቱ ለመጠቀም ረድኤተ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን

## ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት

የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል በአድራሻ ከአሕዛብ ወገን ለሆነው ቴዎፍሎስ የተጻፈ ነው። በዚህ ጽሑፍ ሉቃስ ታሪክን፥ እውነትን፥ የጌታችንንም ትምህርት በጥንቃቄ ከመዘገበ በኋላ ለቴዎፍሎስ እንደጻፈለት እንመለከታለን። የደብዳቤው ዓላማ ቴዎፍሎስ የተማረውን ወንጌል ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ እርግጡን እንዲያውቅ ነው። ስለዚህም የጌታችንን ነገር መናገር ከመጀመሩ አስቀድሞ ስለአዋጅ ነጋሪው ዮሐንስ መጥምቅ ልደት ለመተረክ ከዘካርያስና ከኤልሳቤጥ ሕይወት ይጀምራል።

ዘካርያስ ማለት እግዚአብሔር ያስታውሳል ማለት ነው። ትውልዱ ከቤተ መንግሥት ወገን ሲሆን ከ913–911 ዓ.ዓ. ለይሁዳ የነገሠው የሮብአም የልጅ ልጅ ከሆነው ከአብያ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ወገን ነው (2ኛ ዜና 13)። ይሁን እንጂ ካህን ሆኖ በቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር።

ኤልሣቤጥ ደግሞ ከካህኑ ከአሮን ወገን ናት። ስለዚህ ይህ ቤተሰብ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ጥምር ነበር ማለት ነው። ወንጌሉ እንደሚነግረን ኤልሣቤጥና ዘካርያስ ብሉይ ኪዳን በተገባደደበት ሐዲስ ኪዳን በሚብ ትበት ጊዜ የነበሩ በሕግጋተ እግዚአ ብሔር የሚኖሩ ወይም ትእዛዛቱን የሚፈጽሙ ስለዚህም ነቀፋ የሌለ ባቸው በዓይነት እግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። መካኖችና በዕድሜም የገፉ ነበሩ ይለናል።

በዚህ እኛ ለጊዜው በምንኖርባት ዓለም ይኖሩ የነበሩት እነሉቃስ እውነተኛውን ታሪክ፥ እርግጠኛውን ትምህርት በሚገባ መመዝገብንና ማወቅ ለሚገባው ማሳወቅን ያስተም ሩናል። እውነትን የማያውቅ እውነ ተኛ፤ ታሪክንም የማያውቅ ስለታሪክ ጸሐፊ ሊሆን አይችልም። ቅዱስ ሉቃስ እውነት የሆነውን የሕይወት ትምህርት እርግጥ የሆነውን የመድኃኒታችንን ወንጌል ማወቅ ለሚያስፈልገው ለቴዎፍሎስ ነው የጻፈለት፤ ቴዎፍሎስ ከአህዛብ ወገን የሆነ ለክርስትና ትምህርት እንግዳ በመሆኑ ማወቅና መማር ያስፈልገው ነበርና። በዓለም ላይ ታሪክን እንደታ ሪክነቱ ክርስትናንም እንደክርስትናነቱ የሚመዘግብና ማወቅ ለሚገባቸው ከእግዚአብሔር ለተለዩት አምላካ ቸውን ላላወቁት የምሥራች ላልተ ሰበከላቸው በአርአያ ሥላሴ ግን ለተፈጠሩ የሚጽፍ እምብዛም የለም። የሐሰት ታሪክና የሐሰት ትምህርት ግን ለማስፋፋት የሚበረታ ሞልቷል። የእግዚአብሔር ችግሩ የሚጽፍና የሚያስተምር አይደለም። የእርሱ ችግር እውነትን የሚጽፍ እውነትን የሚናገርና የጻፈውንና የተናገረውን ደግሞ የሚፈጽም ሰው ነው። ስሙን ተሸክሞ የሚሄድ ቃሉን አንግቦ በየሥፍራው ሁሉ እንዲህ ይላል የሚል አልጠፋም። የጠፋው የተሸከ መውን የሚያውቅና እንደ ቴዎፍሎስ ላሉ ማወቅ ለሚገባቸው በሚገባው ሥፍራ ቆሞ የሚናገር የሚናገረውን በገቢር በመፈጸም እንደ ቅዱስ ሉቃስ የሚመሰክር እውነተኛውን፥ ትክክለ ኛውን እርግጠኛውን የሚጽፍ ነው።

ቅዱስ ሉቃስ ታሪካቸውን የጀመ ረላቸው ዘካርያስና ኤልሣቤጥም ከብዙዎች መካከል የተመረጡ እንዲሆኑ ያበቃቸው ነገር አለ። በዘር ሐረግ ከተመረጠ ወገን መሆናቸው አልነበረም ያስመረጣቸው፥ በጥሩ ሕይወት (አኗኗር) መገኘታቸው ነው እንጂ። ኤልሳቤጥና ዘካርያስ መካን ነበሩ። መካንነትም በአይሁድ ዘንድ የኃጢአተኛነት ምልክት ነበር። ይህ ሰው ያየው፥ ሰው የወሰነው ነው። እግዚአብሔር ግን በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ያየው እንዲሆንም የወሰነው አንድ ነገር አለ። አዎን! እነዚህ በአይሁድ ዘንድ የሚታይ ሳይሆን በፈጣሪአቸው ዘንድ የታየ የንጽሕና የቅድስና ሕይወት ነበራ ቸው። ለዚህም ነው ቅዱስ ሉቃስ «በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ» ያላቸው። የዓለም ሁሉ ድካም በሰው ፊት ጻድቅ ሆኖ ለመታየት ነው።ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያልና ሰው ግን በእግዚአብሔር ሊታይ የሚችል ልቡና ሊኖረው ያስፈልጋል።

እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ከነበሩ መካንነታቸው ከኃጢአት እንጂ ከጽድቅ እንዳልነበረ እንረዳለን። እግዚአብሔር ከኃጢአት ምካን የሆኑትንና መካን ለመሆን የተዘጋጁትን የሚያይ አምላክ ነውና። ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ኃጢአተኛ አድርገው ይከንኑ የነበሩት አይሁድ ከእውነትና ከጽድቅ መካኖች ሳሉ በኃጢአት ደግሞ የብዙ ልጆች ወላጆች ነበሩ። እነዚህም ቅዱስ ጳውሎስ በገላቲያ 5 የዘረዘራቸው 16 ልጆች ናቸው። ዛሬም ቢሆን ዓለም የእነዚህ ሁሉ ልጆች እናት ሆና ሰውም አስመስሎ እንዲወልድ የበኩሏን ጥረት እያደረገች ነው። የእነዚህ የፈቃዳተ ሥጋ ወላጆች ወይም አሳዳ ጊዎች በእግዚአብሔር ዓይኖች ለመታየት ዕድል የላቸውም። እነኤል ሣቤጥና ዘካርያስ በአካል የማይታዩ የእገሌ ልጆች ተብለው የማይጠሩ ዘጠኝ ልጆች (ፈቃዳተ ነፍስ) ነበራቸው። እነዚህ በገላትያ 5 ቅዱስ ጳውሎስ ያስቀመጣቸው የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው። በእነዚህ በመመላ ለሳቸውና ከኃጢያት በመለየታቸው ለኃጢአትም መካን በመሆናቸው የእግዚአብሔር ዓይኖች የልቡና ቸውን ንጽሕና የሕይወታቸውን ቅድስና አዩ።

እንግዲህ እግዚአብሔር አሁንም ዓይኖቹ ወደምድርና በውስጧ ወደሚኖሩት ሁሉ ነው። ንጹሕ ልቡና ንና ቅዱስ ሕይወትንም ይፈልጋል። ነገር ግን ዓለማችን ይህንን የሚመስሉ ሰዎች የሏትም። ከኃጢአት መካን የሆነ የለም። ሁሉ ከኃጢአት ወልዷል ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ረክሷል። የዘካርያስንና የኤልሣ ቤጥን ሕይወት አብነት አድርጐ በእግዚአብሔር ፊት በሚታይ ኑሮ እግዚአብሔርን ማምለክ የመረጠ የለም። ራሱን ለቅድስና ሕይወቱን ለጽድቅ የለየ የለም። በዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ነኝ ማለት አይቻ ልም።

ስለዚህ ሁላችን የየራሳችንን ሕይወት ልንመረምር ይገባናል። እነዚያ በአሮጌው ዘመን ፍጻሜ ላይ የነበሩ ኤልሣቤጥና ዘካርያስ ይህን የመሰለ ሕይወት ከነበራቸው እኛማ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በክርስቶስ ደም የተዋጀን፥ አምላካችን የሞተልን የሞት ኃይል የተደመሰሰልንና በነፃነት የምንኖር ምን ያህል ለውጥ በውስጣችን አለ? ምን ያህል በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ ነን? ራሳችንን ከኃጢአት መካን አድርገን በአምላካችን ፊት ለመታየትስ የቱን ያህል ዝግጅት አድርገን ይሆን? በሁሉም ማንነታችንን ስንመረምር ገና ባዶ መሆናችንን እንረዳለን። እውነትን የማናውቅ ለማወቅ ያልተነሳን እውነትን የማንናገር ቢነገረንም ለእውነት የሚገዛ ልቡና የሌለን በኃጢአትና በሥጋ ፈቃዳት ወጥመዶች የተተበተብን ደካሞች መሆናችን ይታወቀናል። ስለዚህ ደግሞ ራሳችንን መለወጥ ማንነታችንን ማደስ የሚገባን መሆናችንን እንገነዘባለን።

በሰዎች ፊት ብቻ የሚወደስ አንቱ የሚባል በእግዚአብሔር ፊት ግን ከንቱ በሆነ ሕይወት መመላለሱ ያብቃና እግዚአብሔር በሚያየው በሚወደው በሚመርጠው በሕጉና በትዕዛዛቱ ጐዳና ለመራመድ እንደፈቃዱም ለመኖር እንዘጋጅ። ያለፈው ባዶነታችን በኃጢያት የተመላለስንበት እግዚአብሔርን ያሳዘንበት ብዙ እጅግ ብዙ በሆኑ ገቢረ ኃጣውዕ የተጠመድንበትና ከእግዚአብሔር ማዳን ተለይተን በሞት ጥላ ውስጥ የነበርንበት የዓለም ሕይወት በንስሐ ታድሶ በምግባርና በሃይማኖት ተቀድሶ የሞተልንን አምላክ እርሱን በፊታችን እየተመለከትን በንፁህ ልቡና ደግሞ በፊቱ እየተመላለስን ፍጻሜ በሌለው ድህነት ለዘለዓለም ሕይወት እንዲሁም ዘካርያስና ኤልሣቤጥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን እንደነበሩ በፊቱ በሚታይ ሕይወት ለሚገኘው የጽድቅ አክሊል እንድንበቃ የእግዚአብሔር ቸርነት የወላዲት አምላክ ረድኤት፥ የቅዱሳን በረከት፥ የመላእክት ጥባቆት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን ✣

## ☆☆☆ ለቈዘመው ☆☆☆

ልጄ ሆይ ታመንከኝ እምነትህን በይቅርታዬና በፍቅሬ ላይ ጣለው። ብዙ ጊዜ ከአንተ የራቅሁ ይመስልሃል። ነገር ግን ምን ጊዜም ከአጠገብህ አልለይም፤ በጣም ቅርብ ነኝ። ሁሉ ነገር ያልተሳካልህ መስሎ የሚታይህ ጊዜም እንዳለ አውቃለሁ። ነገር ግን ልጄ ሆይ ምን ያህል እንደምታምንብኝ ትለካበታለህ እንጂ አትጠፋበትም። አንተ እንዳሰብከውና እንዳቀድከው ባይሰምርልህ ስላልሆነ ወድቀሃል ማለት አይደለም። እንዲሁም ሁኔታዎችን አዝነህና ቈዝመህ ልትመዝናቸው አይገባም። ይልቁንም የወደፊት ሕይወትህ ድቅድቅ ጨለማ የዋጠው መስሎ በሚታይህ ወቅት እንኳን ተስፋ መቁረጥን ከልብህ አውጥተህ ፍፁም ፍቅር ፍርሃትን አስወግዶ ይጥላልና ያንተ ድርሻ የተቻለህን ማድረግ ብቻ ነው። የቀረውን ለእኔ ተወው። እኔ የሠራሁህና እጅግ አድርጌ የማፈቅርህ አምላክህ ነኝ። የልብህ ሐሳብና ምኞት ቁልጭ ብሎ ይታየኛል። ዘለዓለማዊ ደኅንነትህ ትልቅ ፈቃዴ ነው። ስለሆነም በዕለት ሕይወትህ የተዘበራረቀ ሁኔታ ቢገጥምህ እንኳን ለበጐ እለውጠዋለሁ።

ምንም ነገር ከአንተ ብወስድ ጐደለብኝ ብለህ አታጉረምርም። የእኔ ነው የምትለው አንዳች ነገር የለህምና እንኳን ያንተ የሆነው አንተም የእኔ ነህ፤ ሁሉም የእኔ ነው፤ ካለ እኔ ምንም ነህ። ሌላው ቀርቶ ጠንካራ ችግርና መከራን ተከትሎ የሚመጣውን በረከቴን አስብ። ይህም ብቻ አይደለም ማብቂያ የሌለውን ለአንተ ያለኝን ፍቅርና በሕይወት ዘመንህ ሁሉ የምትመራበትን ጥበብ ሁሉ እንደምታገኝ አትዘንጋ። በሕይወትህ በእኔ ፈቃድ ያለፈው ሁሉ አንተ አንተን ከምትወደው በላይ ስለምወድህ የሆነ መሆኑን እወቅ። ስለሆነም በምንም በምን ሁኔታ ውስጥ አታጉረምርም። ከሁሉም በላይ የሆነው ፀጋዬ ይበቃሃል። በርታና በሰላም ተቀበለው። ውጤቱ ደስታና በረከት ሆኖ ታገኘዋለህ።

ምንጩ ያልታወቀ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# እንድደሰትባችሁ

ኢሳይ 1፥10–17

ከባርክ

/የጥዕር ሰም/

ዘመኑ እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት የነበራቸው መልካም ሕይወት ተበላሽቶ ለእግዚአብሔርም ትዕዛዛት ባለመገዛታቸው ፈጣሪአቸው አብዝቶ ያዘነበት ነበር። መሪዎችም ሕዝቡን ለመምራት የሚያስፈልገውን የእግዚአብሔርን ሕግ የተላለፉበት ወቅት ነበርና እግዚአብሔር በነቢያት አንደበት ሕዝቡን ይገስፅ ነበር። በዚያ ዘመን ከነበሩት ነቢያት መካከል ኢሳይያስ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ያስተላለፈውን ተግሣፅ ነው የምን መለከተው። ሕዝቡ በአምላኩ ፊት መልካም መንገድን ትቶ ልቅ በሆነ ሕይወት ይኖር ስለነበረ እግዚአብሔር አብዝቶ እንዳዘነበት ቃሉ ይነግረናል። ከዚህ የእግዚአብሔር ሀዘን የተነሣም ቁጣው መቃጣቱን እናስተውላለን። ነቢዩ ይህን መልእክት የተናገረውም በሕዝቡ በደል ምክንያት ፈጣሪ መዓቱን ከማውረዱ አስቀድሞ በንስሐ ይመለስ እንደሆን ለማስጠንቀቅ ነው። በማስጠንቀቂያው የእግዚአብሔርን ሕግ አድምጡ ይላቸዋል። ቀድሞውኑ አባቶቻቸው እንደአደረጉት ሁሉ መስዋዕት ሲሰው፤ የተለያዩ መባዎችን ሲያቀርቡ እንደነበረና እግዚአብሔር ግን በእነዚህ ሁሉ እንዳልተደሰተ፤ በልምድም ለመታየት ብትመጡ በቤተ መቅደሴም ብትቆሙ ለእኔ ምን ይጠቅመኛል–በዚህ ሕይወት በሌለበት መመላለሳችሁስ የሚደሰት ማነው? በላይ ያማረና መልካም የሆነ ውስጡ ግን ምናምንቴ (ርኩስ) የሆነ ቁርባናችሁን ወደእኔ ብታመጡ በእኔ ፊት የረከሰ ነው። በሕይወታችሁ መታደስ ሳይኖር በልማድ ለእኔ የምታጥኑት በኃጢአት የሚቀርብ ዕጣናችሁ ሌላውም የምታደርጉት ነገር ሁሉ በፊቴ የተጠላ ነው፡- መሰብሰባችሁም ለነገርና ለሐሜት ለአሉባልታ በመሆኑ በዚያ ሆናችሁ እጃችሁን ወደእኔ ብትዘረጉ አላያችሁም፡- ብትጮኹም አልሰማችሁም ሰውነታችሁ ኃጢአትን ተሞልታለችና። ስለዚህም አስቀድማችሁ ታጠቡ፥ ሰውነታችሁን አንጹ፥ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፥ ክፉ ሃሳባችሁን ተው፥ መልካም መሥራትን ተማሩ፥ እውነተኛውን ነገር ፈልጉ በማለት በሕይወታቸው ውስጥ ስለአለው የማይገባ ነገር ገልጦ ሲገስፃቸው እንሰማለን።

ያ እንዲህ የተነገረበት ሕዝብ የእግዚአብሔርን አምላክነት የረሳ የራሱን መንገድ በፊቱ ያዘጋጀ እውነትንና የጽድቅን ነገር የተወ ስለሥጋው ፈቃድ ብሎ ከፈጣሪው ጋራ የተጣላ ነበር። በዚህ መረን በሆነ ሕይወቱም የሚሠራው አጥቶ እጅግም አብዝቶ በዝሙትና በጣዖት አምልኮ የእግዚአብሔርንም ቤት በማርከስ አምላኩን ያሳዘነ፡- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ንቆ በራሱ የድካምና የውርደት፡- የኃጢአትና የሞት ጎዳና የተጓዘ ክፉት ቤቱን የሠራበት ሰይጣንም ግዛቱን ያስፋፋበት በኑሮው ሁሉ መልካም ነገር ያልተገኘበት ሕዝብ ነበር።

ስለበደለው በደል አልቅሶ ከኃጢአት ኑሮው ተመልሶ ከፈጣሪው መታረቅ በሚገባው ሰዓት እግዚአብሔርን ለማታለልና ለመደለል በመሞከር በማይገባ አገላለጥና በማስመሰል የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል በቤተ መቅደሱ ይገኛል ፈጣሪ የውጭውን ብቻ ሳይሆን የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚያውቅ መሆኑን በመዘንጋት። ለታይታ መስዋዕት፡- ጸሎትን፡-ዕጣንን፡-በቤተ መቅደሱ ይዞ ይመጣ ነበር፡- ነገር ግን ውስጡ ልቡ የጠመመ ትውልድ ስለነበረ እግዚአብሔር በዚህ ደስተኛ አልነበረም፡- ያስቆጣውም የመዓት እጆቹን እንዲዘረጋ ያስነሳውም ይህ የሕዝቡ ተንኮል ነበር።

ከዚህ ይልቅ ለእግዚአብሔር ደስ የሚለው የሚታየውና ለታይታ በሰው ፊት የሚቀርበው ፍቅር አልባ መስዋዕትና ዕጣን ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያየው ንጹሕ ልብ ከፍፁም ፍቅርና ከእውነተኛ ሕይወት ጋራ የሚቀርበው መስዋዕት ነው። ይህ ስጦታ ምን መሆኑን እንዴትም ለእግዚአብሔር እንደሚቀርብ ከዚያ ሕዝብ አእምሮ የተሠወረ ምስጢር ነበር። ማስተዋልና ደግነት በውስጡ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ስላልነበረ ለእግዚአብሔር የሚታይ የሕይወት ስጦታ በመታጣቱ ያ በደለኛ የተባለ ሕዝብ ከፈጣሪው ጋራ ተጣልቶ ወቀሳና ተግሣፅ ሲነገርበት እንሰማለን። ይህም ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ወደ እኔ መምጣታችሁ በትህትና ሳይሆን በትዕቢት፥ እኔን በመፍራት ሳይሆን በድፍረት፥ በሥጋ ለባሹ ሰው ፊት ለመታየትና ለመሞገስ ከሆነ – ከምስጋናችሁ ጋራ ሐሜትና አሉባልታ፥ ከጸሎታችሁ ጋራ ጥልና ክርክር፥ ከመስዋዕታችሁ ጋራ ቂምና በቀል ከተመረጠው ዕጣናችሁ ጋራ ክፋትና ተንኮል ደባልቃችሁ ብታቀርቡልኝ የሚያስደስተኝ አንድ ስንኳ ነገር የለም። የምታጥኑልኝ ዕጣን በኃጢአት የተቀመመ ከሆነና በንጹሕ ልብ ካልቀረበ በፊት መልካም አይደለም። ሽንገላ የተሞላበትና በእውነት ላይ ያልተመሰረተው መሰብሰባችሁ ከመጀመሪያ አንስቶ እስከፍጻሜው ድረስ የጽድቅ ዓላማ የሌለው በመሆኑ አያስደስተኝም። ጩኸታችሁም በኃጢአት ከተሞላ ውና ለንስሐ ካልተዘጋጀው ደንዳና ሕይወታችሁ የሚወጣ በመሆኑ አልስማችሁም ይላቸዋል።

በእኔ ፊትም ሞገስን ታገኙ ዘንድ ጥሪአችሁ እንዲሰማ– ፊታችሁንም እንዳይ በነፍሳችሁ ታጠቡ፤ በእግዚ አብሔር ፊት አስፀያፊ የነበረው ሕይወት ይታደስ ዘንድ ክፉውን ሃሳብና ፈቃድ ትተው በአንደበትና ለታይታ ብቻ የእግዚአብሔር ሰው መስሎ መታየቱና መመላለሱ በፍጹም እንዲለወጡ እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት ሲነግራቸው ተመለከትን።

እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሆነ ሕዝብ በእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዛት ሊጓዝ ይገባዋል። ለእግዚአ ብሔር ሕዝብ ምልክቱ አምላኩን አውቆ በሕጉና በትዕዛዛቱ በመመራት በቅድስና የሚታዘዘውን እየፈጸመ መኖር ነው እንጂ ሽንገላና ማስመ ሰል፤ ፌዝና በዓለም ባህር ተዘፍቆ የሕይወት እንቆቅልሽ መጫወት ይልቁንም ደግሞ ለእግዚአብሔር ደስ በማያሰኝ የማይጠቅም ሕይወት መመላለስ አይደለም። ከዚህ በመነሳት በዚህ ዘመን የምንኖር የእግዚአብሔር ወገኖች ነን የምንል የሰው ዘሮች በዚህ የትንቢት ቃል ሕይወታችንን ብንመረ ምር የእኛ ኑሮ በእግዚአብሔር ፊት ምን ይመስል ይሆን?

ከመካከላችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሕግ እንደትዕዛዛቱም የተራ መደና የሚራመድ ማን ይኖር ይሆን? ፍፁም የሆነና በሃይማኖት የሚቀርብ የሕይወት መስዋዕትስ በእግዚአብ ሔር ፊት የሚሰዋ ማነው? በውኑ በእግዚአብሔር ቃል የለዘበ ለሕግጋቱ የታዘዘና ንፁሕ የሆነ እግዚአብሔርም የሚደሰትበት የንጹሕ ልብ መስዋዕት ይዘን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ቀርበን እናውቅ ይሆን? ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንጓዝ እግዚአብሔር ብቻ እንዲ መለከተን በትሕትና ሸማ ተጎናጽፈን የፍቅርን ጫማ ተጫምተን በዚህ ዓለም ላይ አሉ የምንላቸውን ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት ቢደረጉ የሚገባ ቸውን የፍቅርና የእምነት እንዲሁም የትዕግሥትና የንጽሕና ጌጣጌጥ አጊጠን የቀረብን ከቶ እነማን እንሆን?

ለእግዚአብሔር በምናቀርበው ስጦታ ሁሉስ በረከት እናገኛለን ብለን ያለጥርጥር አምነን፤ በጸሎታችንስ ሐሜትና አሉባልታን ሳናስገባ ጠብንና ክፋትን ሳንቀላቅል የምንሰጥ፤ መሰብሰባችንስ ከበደልና ከኃጢአት የራቀ እግዚአብሔር ብቻ የሚመሰገን በት፤ እርሱ ያከበራቸው ቅዱሳን የሚታሰቡበት ንፁሕ የሆነ የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምበት የሆነ እነማን እንሆን?

ከእኛ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር በእውነተኛ ሀዘን የሚቀርብ በፍቅርና በእውነት የመጸጸትም የሚጸልይ ማን አለ? በኃጢአቱስ ላይ በእውነተኛ ለቅሶ የሚናዘዝ ማነው? የሁሉም ሰው ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት መልካም አልሆነም። በዚህ ዘመን ለእግዚአብሔር ሕግጋት የሚገዛ ሰው አልተገኘም፤ ሁሉም ቢሆን እግዚአ ብሔር ከሰጠው ሕግ ሌላ ለሥጋውና ለዓለማዊ ፈቃዱ የሚመች የራሱ ሕግ ሠርቶ አምላክ ከሚፈልገው የሕይወት ጎዳና ተለይቶ ይገኛል። በንጹሕ ልቡናው ወደፈጣሪው የሚቀርብ ማንም የለም። የሁላችንም ልቡና በኃጢአት የተበከለና በእግዚአብሔር ፊትም የረከሰ ስለሆነ በእኛ ሥራ እግዚአብሔር አልተደሰተበትም። ወደ ቤተ ክርስቲያንም ስንጓዝ ለሰው ለመታየት አባ አባ ለመባል እንጂ በእግዚአብሔር ዓይን የሚታይ አንድ ስንኳ ሥነ ምግባር የለንም። ያለአግ ባብ ሆነን በደጁና በመቅደሱ በመመላለሳችን ከእኛ ሕይወት እግዚአብሔር የሚሻውን ፍሬ ሃይማ ኖትና ምግባር አላገኘም። በቤተ ክርስቲያን የምናቀርበው መባዕ እና



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የምስጋና ስጦታ ሁሉ በኃጢአት ተዳድፈን የምናቀርበው ነውና ፈጣሪ አችን በዚህ አይደሰትበትም። ስለዚህም ይህን የመሰለውን ስጦታ ይዘን ወደፊቱ መቅረብ የለብንም።

በተሰበሰብን ጊዜ ሁሉ የእግዚ አብሔርን ክብር ከመናገርና የቸርነቱን ነገር ከማድነቅ ይልቅ፥ ስለራሳችንም ኃጢአት እያሰብን ከመጸጸት የምን መርጠው ስለሰው ክብርና ዝና እንዲ ሁም የኃጢአትን ነገር ማውራትን በመሆኑ አምላካችን እግዚአብሔር በመሰብሰባችን አይደሰትም። ይህን የመሰለውን የክርስቲያኖች ስብሰባም አይወድም። የክርስቲያኖች መሰብሰባ ቸው ለጽድቅ፥ ለምስጋና ነው እንጂ ለአሉባልታና ለሐሜት አይደለምና።

እንግዲህ እስከመቼ በእግዚአ ብሔር ትዕዛዛት ላይ በማፊዝ፥ በፊ ቱስ በሽንገላ እንመላለሳለን? እስከመቼስ ኃጢአት የተደባለቀበት፥ ከፉ ምኞት የሞላበት ስጦታ ይዘን ወደ ፈጣሪአችን ፊት እንቀርባለን? መሰብ ሰባችንና ዕጣናችን መስዋዕታችንስ ጨኸትና ልመናችንስ እስከመቼ ድረስ የረከሰ ይሁን? እንግዲህስ ይበቃናል። በቆሸሸና በረከሰ ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት መመላለስ የሚ ጠቅም አይደለም። በዚህ ሕይወት የተመላለሱ አልተጠቀሙምና ልንመ ለስ፥ ልናለቅስ፥ ራሳችንን ልንመረ ምር፥ ጩኸታችንን ለእግዚአብሔር ጆሮ እንዲጥም አድርገን ልናለዝብ፥ ስለኃጢአታችንና ስለበደላችን ሁሉ በእውነት ልናለቅስ ይገባናል። ለዚህ ደግሞ ጊዜው አሁን ነው። ሳንመለስ ቀርተን በዓለም ፈቃድ ተይዘን ስናመነታ የእግዚአብሔር ትዕግስቱ ያበቃ እንደሆን ሥጋዊው ምኞታችን ይዞን እንዳይጠፋ በማስተዋልና በጥበብ ዘመኑንም እየዋጀን መመላለስ የሚያስፈልግበት ሰዓቱ አሁን ዛሬ ነው።

በእግዚአብሔር ፊት እንደሚገባ የተመላለሱ ሕጉን የጠበቁ፥ በእውነትና በፍቅር ያመለኩት እውነተኛውን የንፁሕ ልብ መስዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረቡት ዕጣኑን በፍቅር ያጠኑለት፥ ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ፊት ቅን ያደረጉ፥ በኃጢአታቸውም በእውነትና በእም ነት የተናዘዙ ቀደምት አበው እነርሱ የሕይወት አክሊላቸውን የእረፍት ሕይወታቸውን አግኝተዋል። እኛ ደግሞ የዚህን ሕይወት ዋጋ እንዳናጣ ከእውነት መንገድ እንዳንወጣ፥ ከፈጣሪአችን እንዳንለይና ወደውጭ እንዳንጣል ራሳችንን ማስተካከል መንፈሳዊ ሕይወታችንን ማደስና መለወጥ አለብን። ከኃጢአት እድ ፋችን መታጠብ አለብን፤ ከመንፈስ እርጅናችን መታደስ አለብን፤ የእግዚአብሔር ከሆንን አዲሶች ነንና እንደገና ወደዓለም ጭቃ መመለስ አያስፈልገንም። ስለዚህ የእስከዛሬው የዓለም ኑሮ ይበቃን! እስከዛሬም ከአምላካችን የተለየነው፥ የተቅበዘበ ዝነው ይበቃናል።

እንግዲህ በንስሐ ውኃ መታጠ ብና ንጹሐን ሆነን ለአምላካችን ዘወትር ንጹሕ የምስጋና መስዋዕት የምንሰዋ፥ በፊቱም በየዋሕነትና በቅንነት በጥበብና በፍቅር የምን መላለስ መሆን ይገባናል። እግዚአ ብሔር በሽንገላ የሚደለል አምላክ አይደለምና በእውነት በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን መሆን አለብን፤ እናም ከአሁን ወዲያ ሰውነታችን መንጻት ይገባዋል። ክፉ ሥራችን መቅረት አለበት፤ መልካም መሥራትን የጽድቅን ነገር መማርና በዚህ ሕይወትም መኖር አለብን፤ ሥጋችንንና የሥጋ ጥበባችንን ብቻ የምናመልክና የምንወድ ለሥጋ ገበያም የምንጣደፍ መሆን የለብንም። ከአሁን በኋላ ጊዜው የነፍስ ነው፤ የጽድቅ ነው፥ የፍቅር ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በፊቱ ለእርሱ ደስ በሚያሰኝ ፍጹም እምነትና በቀና ሥነ ምግባር በሥርዓተ አበው ለመመላለስ እንድንችል በንስሐ ታጥበን የሥጋውና የደሙ ተመጋቢዎች የክብሩም ወራሾች እንዲያደርገን እርሱ በቸርነቱ ቅድስት ድንግል እመቤታችን በአማላጅነቷ ቅዱሳንም በረድኤት ከሁላችን ጋራ ይሁኑ። አሜን። ❖

ወይትባረክ እግዚአብሔር።

> ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፤ በፍለጋውም እንሔዳለን ይላሉ።
>
> ሚክ 4፥2።
>
> ወደ እግዚአብሔር ቤት እን ሒድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ።
>
> መዝ101፥1።
>
> ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን፤ ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል።
>
> መዝ 94፥1።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ማነው እውነተኛ

አምላኩን የሚወድ ታማኝ ለፈጣሪ፥
ሁሉን እኩል የሚያይ በእውነት አፍቃሪ፥
የአፍ ሰው ያልሆነ ያይደለ ዳተኛ፥
ክርስቲያን ነኝ የሚል ማነው እውነተኛ?
ከተንኮል የራቀ ክፋት የሌለበት፥
የሸንገላ ከንፈር የማታለል ፍቅር ቤቱን ያልሰራበት፥
ወንድሙን እህቱን በፍፁም አፍቃሪ፥
ማነው እውነተኛ ታዛዥ ለፈጣሪ?
ማለዳ ተነስቶ ሰውን የማያማ፥
በአምላክ ቸርነት በይቅርታው ሥራ ከቶ ያላቅማማ፥
ያመነ በእውነት ጥርጥር የራቀው፥
የእግዚአብሔር ወዳጅ እውነተኛ ማነው?
በወንጌል ገበታ በወንጌል አውድማ፥
በፍቅር የሚፀልይ ሰውን የማያማ፥
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በፈጣሪ ቅጥር፥
ሰውን የማይጠላ ሰውን የሚያፈቅር፥
ቃሉ የታመነ እግዚአብሔርን የፈራ፥
በእውነት የሚጓዝ እውነት የሚሠራ፥
ቅን ልቡና ያለው ከሸፍጥ የተለየ፥
ማነው እውነተኛ የአምላክን ቸርነት በሃይማኖት ያየ?
ማነው ያስተዋለ ሁሉን የመዘነ፥
አምላክ ስለራቀን በእውነት ያዘነ።
ፍቅር ስለጠፋች ማነው የፈለገ ማን ይህን አወቀ፥
ሐሜት አሉባልታን ያልለበሳትና ከሐሰት የራቀ።
ዓይኑ ከሰው ይልቅ የራሱን ያየለት፥
ሰውን የማይፈትን ሰው የማያሳስት።
ስለፍቅር ብሎ በደልን የተወ ወንድሙን ያልጠላ፥
አንዴ በመሸንገል አንዴ በማታለል በእምነትና ክህደት በሁለት ያልበላ።
እራሱን አፅድቆ ሌላውን ያልናቀ፥
ማነው የወንጌል ሰው እውነትን ያወቀ?
ዘወትር በኑሮው ሕይወቱን መርማሪ፥
ከሚሆነው ሁሉ በፍቅር አስተዋይ በፍቅር ተማሪ።
ከፋት የማያውቀው የቅናት መጋኛ፥
የመውደድ ባለቤት የታለ ክርስቲያን ማነው እውነተኛ?
ምክርን ያፈቀረ ተግሳፅን የሰማ፥
ቁጣን የወደደ ትምህርት የተጠማ፥
በደሉን ያወቀ ቁስሉ የዳነለት፥
አምላኩን ያመነ ፍፁም በመጸጸት፥
ጥበብን ፈላጊ ጥበብን አንባቢ፥
በሕይወቱ መምህር የሰው ሕይወት ገንቢ፥
አምላኩን ከራሱ ሂድልኝ ያላለ፥
በትዕቢቱ ወድቆ ከቶ ያልቀለለ።
የእውነት ተማሪ የእውነት አዳማጭ በአሉባልታ ወሬ ፍፁም ያልታለለ፥
ክርስቲያን ነኝ የሚል እውነተኛ ነኝ ባይ ይነሳ የትአለ?
ዳሩ ሰው መሳዮች ዳሩ ዘማሪዎች
ለሚያዩን ተዋዳጅ ፍፁም ክርስቲያኖች
ዘወትር የምንደክም ጌታን ለመደለል፥
ውሸት እየወራን ስንምል በገብርኤል፥
ፍቅርን ሳንፋቀር እኛን ሳንመረምር፥
ይመስለን ይሆናል ይህ ጩኸት ተሰምቶ መልስን የምናገኝ፥
ቁርጣችንን አውቀን ነገ ዛሬ ሳንል በንስሐ እንንፃ ይልቅስ እንምኝ።
ማንንም አናታል በከንቱም አንልፋ፥
በሐሰት አይገኝም እውነተኛው ተስፋ።
ይልቅስ እናንባ ይልቅስ እናልቅስ፥
ሰው መብላቱን ትተን ራሳችንን እንውቀስ።
ይልቅስ እንማር ይልቅስ እናንባ፥
እኛን ሜዳ ጥለን በሰው ቤት አንግባ።
ይልቅ ተመለሱ ይልቅ እንመለስ፥
ተግሣፅን እንስማ ነፍሳችን ትወቀስ።
ይህ ሁሉ ሲነገር ይህ ሁሉ ሲነበብ፥
ራሱን ያጠና ሰው የነበር በጥበብ፥
ስለሆነው ሁሉ ራሱን የጠየቀ ራሱን የወቀሰ፥
በዚህች አጭር ቅፅበት ጌታን ያስታወሰ፥
በአንዱ ጆሮው ሰምቶ በሌላው ያልተኛ፥
ወንጌልን የሚወድ የፍቅረ ቢፅ ጀግና ማነው እውነተኛ?
ራሳችን ይነሳ እንግዲህ እንንቃ ዘለዓለም አንተኛ፥
ሁል ጊዜ አንወቀስ አንሁን ቸልተኛ፥
ቸሩ ፈጣሪያችን ማስተዋልን ይስጠን ያርገን እውነተኛ።

✤

ወለእግዚአብሔር ስብሐት

ካዘና ይገባል

/የብዕር ስም/



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ሀ. ስለ ልሳን መጽሐፍ ቅዱስን እንበበዋል?

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያስተውሏቸው።

«ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ...»

ማር.16፥17

«በአንዱ መንፈስ...ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፤ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል...»

1ኛ.ቆሮ 12፥10

«በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤...»

1ኛ.ቆሮ 14፥2

«ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር።»

1ኛ.ቆሮ 14፥5

«በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም።»

1ኛ. ቆሮ 14፥27

«በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ»

1ኛ.ቆሮ 14፥39

በቁጥር 2 እትማችን በልሳን ስለመናገር ሰፊ ትምህርት አዘጋጅተንላችኋል።

ለ. ቅዱስ መጽሐፍ ስለፀበል ምን እንደሚያስተምር ያውቃሉ? መልሱን ከቁጥር ሁለት እትማችን ታገኙታላችሁ።

# ሐመር

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡